# ክፍል 2 - የእግዚአብሔር አንድነት በሦስትነት

## ምዕራፍ 25 - ምሥጢረ ሥላሴ

«ከአባቶች መምህራን ሲነገርም ‹ምሥጢረ ሥላሴን› ጠልቆ ለማወቅ መሞከር ባሕረ ውቅያኖስን በዕንቍላል እየቀዱ ለመጨረስ እየጨለፉም ለመጨለጥ እንደ ማሰብ ነው ይላሉ» (1)። እውነት ነው፤ ለሰው ከተሰጡት ሥራዎች ምሥጢረ ሥላሴን ከመመርመር የሰፋና የከበደ የለም። ሆኖም ስለ ሥላሴ በትክክል ማሰብ ለክርስቲያናዊ ኑሮ ዋና መሠረት ነው። ምክንያቱም ሰው በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲጠመቅ፥ ከሦስቱ አካላት ጋር ተገናኝቶ እነርሱን ያመልካል፤ ሕይወትንም ከእነርሱ ይቀበላል፤ በእነርሱ ስም ይባረካልና ለእነርሱ ይኖራል።

አይሁድ፥ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች አንድን አምላክ ሲያመልኩ፥ የሥላሴን ትምህርት በአንድ አምላክ ከሚያምኑ ሌሎች ሁሉ ክርስቲያኖችን ይለያቸዋል። ስለዚህ ክርስቲያን ለራሱ ብቻ ሳይሆን የራሱን እምነት ለሌሎች ለመግለጥም የሥላሴን ትምህርት ማወቅ ይገባዋል።

ሥላሴ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን አይገኝም። በግእዝ ቋንቋ ቃሉ «ሦስትነት» ማለት ነውና በትምህርተ መለኮት ጥቅም ላይ ሲውል በአንዱ እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንዳሉ ያሳስባል። በ2ኛው መቶ ዓመት የአንጾኪያ ጳጳስ የነበረው ቴዎፍሎስ በግሪክ ቋንቋ «ትሪአስ» እና ተርቱሊያን በላቲን ቋንቋ «ትርንታስ» (በእንግሊዝኛ TRINITY) ስለ እግዚአብሔር ሲያስተምሩ፥ የአካላትን ሦስትነት ለማመልከት ተጠቀሙባቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምረው የቤተ ክርስቲያን አባቶች በእነዚህ ቃላት እየተጠቀሙ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ለማብራራትና ለመወሰን ሰፊ ጥረት አደረጉ። እንደ እነዚህ ቃላት ሁሉ ሥላሴ የሚለው ቃል ስለ እግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የሚሰጠውን ትምህርት ያመለክታል።

ሥላሴ የሚለው ቃልና ትምህርቱ እንደ መነጥር ሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው ትምህርት ጉልሕ ሆኖ እንዲታየን ያደርጋሉ እንጂ በእግዚአብሔር ቃል ላይ አዲስ ትምህርት አይጨምሩም። ትምህርተ ሥላሴ ለክርስቲያን ረቂቅ ፍልስፍና አይደለም፤ ይህንም ለማስተዋል የሚከተለው ምሳሌ ሊረዳን ይችላል።

የአንድ ሕፃን ወላጆች ቢሞቱ፥ ሌላ ቤተሰብ ሕፃኑን ተቀብሎ ወደ ቤቱ ይወስደዋል። በቤተሰቡ ውስጥ አባት፥ እናትና ምናልባት አንድ ወይም ሁለት ልጆች ሊገኙ ይችላሉ። ሕፃኑ ወደዚያ ቤተሰብ ቤት ከመግባቱ በፊት በቤተሰቡ መካከል ኅብረት፥ ፍቅር፥ ሥርዐት ...ወዘተ ነበረ። ሕፃኑም ሲገባ በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ይሳተፋል፤ በኅብረቱ፥ በፍቅሩ፥ በሥርዐቱ ...ወዘተ ያድጋል። እያደገም ሲሄድ ስለ ቤተሰቡ አባት፥ እናትና ሌሎች ልጆች እያስተዋለና እየተደሰተ ይሄዳል። ሰው «ዳግመኛ ሲወለድ» ወደ ቅድስት ሥላሴ ኅብረት ይገባል፤ በእነርሱ ይወደዳል፤ ልጅነቱንም ማስተዋል ይጀምራል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሁኔታ፥ «አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነትን መንፈስ ተቀበላችሁ ...» እና «ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ» በማለቱ አማኙ በአምላካዊ ኅብረት መሳተፉን ያሳያል፤ በዚህም ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከአማኙ ጋር ይገናኛሉ፤

ሮም 8፥15፤ ገላ. 4፥6 (2)። በሐዋርያው ትምህርት መሠረት የክርስቲያን ኑሮ ከዓለም አኗኗር ይለያል፤ ክርስቲያንም በክርስቶስ ይኖራል፤ አዲስ ፍጥረት ነው፤ አገሩም በሰማይ ነው፤ ገላ. 2፥20፤ 2ቆሮ. 5፥17፤ ፊል. 3፥20። ሐዋርያው ዮሐንስ፥ «ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው» ያለውና «ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ ... ተሰፋ ሰጥቶናል» በማለት ሐዋርያው ጴጥሮስ የተናገረው ከጳውሎስ ትምህርት ጋር ይስማማሉ፤ 1ዮሐ. 1፥3፤ 2ጴጥ. 1፥4 አ.መ.ት.። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መንፈስ ቅዱስ ከተከታዮች ጋር እንደሚኖር ካስተማረ በኋላ፥ «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም እንመጣለን፤ በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» በማለት አማኙ የሦስቱን አካላት ፍቅር እንደሚያውቅ ያሳያል፤ ዮሐ. 14፥17:23። ከደገና ቤተሰብ የተወለደ ልጅ የአባቱንና የእናቱን አንድነትና ልዩነት፥ እንደዚሁም የሚያደርጉለትን እንክብካቤ ሁሉ እያደገ ሲሄድ እንደሚያውቅ ሁሉ፥ ክርስቲያንም በመንፈስ እያደገ ሲመጣ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት፥ እንደዚሁም የሦስቱን ሥራ (ግብር) ለራሱ እያስተዋለ ይሄዳል፤ በሥራቸውም ይገረማል፤ ይደነቃል፤ ያመሰግናልም። ክርስቲያን ይህን ሲያደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትምህርተ ሥላሴ የሚሰጠው ትምህርት ሕያው መሆኑን በማረጋገጥ ይደሰትበታል እንጂ አድካሚ ሆኖ አያገኘውም፤ ምክንያቱም በሥላሴ ዘንድ ይኖራል፤ ሥላሴም በውስጡ ያድራል።

ትምህርተ ሥላሴ እንደ ውቅያኖስ ነው ተብሏልና አንባቢው በእርሱ ከመዋኘቱ በፊት አንድ አፍታ ቆም ቢልና ወደ ላይ ቢመለከት ተገቢ ነው። ቀጥሎ ለመዋኘት እንዲችልም ትምህርቱን በፀጥሩ ለመዘርዘር የሚከተለው ትንታኔ ምናልባት ይረዳዋል።

## ሀ) ትምህርተ ሥላሴ በፀጥሩ

ውቅያኖሱን በአራት ድምበሮች ለመወሰን እንሞክራለን። ዋናተኛ ሲጀምር፥ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ እግዚአብሔር አካላዊ ነው፤ ሦስት አካላት በአንዱ እግዚአብሔር አሉና ሦስቱ አካላት የግል ተግባራት አሏቸው የሚሉትን አራት ነጥቦች ቢያስተውል ጥሩ ነው። ከዚያም በኋላ ትምህርቱን እንደሚከተለው ቢተነትን አይሰጥምም።

1. አንድ አምላክ ብቻ አለ (ሦስት አማልክት የሉም)።

2. የአንድ አምላክ አንድነት ምሥጢራዊነት አለው፤ ምክንያቱም በአንዱ አምላክ ውስጥ ሦስት አካላት አሉ፤ በግንኙነታቸው ሁኔታ መሠረትም በመጽሐፍ ቅዱስ አብ (አባት)፥ ወልድ (ልጅ) እና መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ) ተብለዋል። በሦስቱም መካከል «እኔ»፥ «አንተ» እና «እርሱ» መባባል አለ። ሦስቱም ከዘለዓለም ናቸው፤ ሦስቱም በመለኮት፥ በክብር፥ በባሕርይ፥ በባሕርይ መገለጫዎች አንድ ናቸውና በህልውናቸው (በመኖራቸው፥ በመሆናቸው) አይበላለጡም፤ መብለጥ ወይም ማነስ በመካከላቸው የለም። እግዚአብሔር አይከፋፈልምና እነርሱ የእርሱ ሦስት ክፍሎች አይደሉም ወይም በአንድ ክበብ ውስጥ እንደሚገኙ ሦስት አባላት አይደሉም። አንዱ ያለ ሌሎች ሁለቱ አይኖርም።

3. አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአጠራራቸው ቅደም ተከተል እንዳላቸው ሁሉ፥ በሥራቸውም (በግብራቸው) ቅደም ተከተል አላቸው። በግብራቸው የሚታየው ቅደም ተከተል አብ ወልድን ይልካል፤ በወልድ አማካይነት መንፈስ ቅዱስንም ይልካል። ወልድ የአብን ፈቃድ ይከተላል፤ ከአብ የተቀበለውን መንፈስ ቅዱስንም

«እነርሱ ግን ዐመፁ፤ ቅዱስ መንፈሱንም አስመረሩ» (ኢሳ. 63፥10) የሚለው ጥቅስ የአንድን አካል ኀይል ማሳዘን ባለመቻሉ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ አካላዊ መሆኑን የሚያረጋግጥ እንደሆነ ያምናሉ። እንደዚሁም ከእግዚአብሔር የሚላከውና እንደ እግዚአብሔር የሚቈጠረው የእግዚአብሔር መልአክ የራሱ አምላካዊ አካል ያለው ይመስላል፤ ለምሳሌ ዘጸ. 3፥2:6 ይመ. (ም.33 ስለ መላእክት ለ.5 ይመ.)።

ሰ) ስለ ምሳሌ 8፥22-31 አተረጓጐም ብዙ ክርክር አለ። የመጀመሪያዎቹ ቍጥሮች ጥበብን በሰውኛ አባባል የሚገልጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም፥ «የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ፥ የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ፤ ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ ...» (ቍ. 30) ከሰውኛ አባባል ዐልፎ አካላዊ ምስክርነት መሆኑን ብዙዎች ያስባሉ፤ አንዳንዶችም ሥጋ ሳይነሣ እግዚአብሔር ወልድን ያመለክታል ይላሉ። እንደዚህ ከሆነ፥ «አንቀጹ ወልድ እንደተፈጠረ አያሳይምን?» የሚለውን ጥያቄ ያስነሣል። ችግሩ የተፈጠረው ከሰባው ሊቃናት ግሪክ ትርጕም ይመስላል። እነርሱ «አገኘ» ወይም «ለራሱ አደረገ፤ ተጠቀመ» ተብሎ ብዙ ጊዜ የሚተረጐመውን የዕብራይስጥ ግሥ «ፈጠረ» በሚል የግሪክ ቃል ተረጐሙት። በተለመደው ዐይነት ቢተረጐሙት ኖሮ እግዚአብሔር በወልድ ችሎታ በፍጥረት ሥራ ተጠቀመ በማለት አንቀጹን ማስተዋል ይቻል ነበር። ሆኖም በሌላ ዘንድ የመጽሐፉ ጸሓፊ ስለ ጥበብ (ም. 8፥1-12) እና ስለ ስንፍና (ም. 9፥13-18) በሰውኛ አባባል በስፋት ስለሚጠቀም፥ (8፥22-31) የእግዚአብሔርን ልጅ የሚያመለክት ለመሆኑ በቂ ምክንያት የለም ማለት ይሻላል (7)።

ይህን ክፍል ስንደመድም ስለ ቅድስት ሥላሴ በብሉይ ኪዳን ከሚገኘው ትምህርት አራት ነጥቦችን መገንዘብ ይገባናል።

1) በአበውና በሌሎች ሊቃውንት የሚሰጠው ትምህርትና የጥቅሶቹ አተረጓጐም እጅግ የተለያየ ነው።

2) አይሁድ ብሉይ ኪዳንን ሲያነቡ መሲሑን ይጠባበቁ የነበረው፥ ከእግዚአብሔር እንደተላከ ሰው እንጂ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ሰው አልነበረም።

3) እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥ ብዙ ጊዜ አስቀድሞ ትንቢት ይሰጣል፤ ከዚያም በኋላ በልዩ ሥራና ከሥራው በኋላ በሚልካቸው ሰዎች ትምህርተ አስተርእዮን ይፈጽማል (ም.2 እና ም.5 ይመ.)። ስለዚህ ቃል ሥጋ ከሆነ በኋላና መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ ሦስት አካላት በአንድ አምላክ ተገለጡ። በሌላ አነጋገር የክርስቶስ ሥራ በግልጥ ሳይታወቅ፥ ትምህርተ ሥላሴን በሰፊው ለመመርመር መሞከር የአስተርእዮን ግብ አለማስተዋል ነው።

የሥላሴን አገላለጥ ከሰው መዳን ነጥለን ማየት አንችልም። አብ ለኀጢአታችን መሥዋዕትን እንዲያቀርብ ወልድን ላከ፤ ወልድ ከአብ ቍጣና ከሕግ ባርነት በደሙ ዋጀን፤ መንፈስ ቅዱስም ወደ ልባችን ገብቶ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን «አባ አባት» ብለን እንድንጮኽ እምነት ይሰጠናል፤ ገላ. 4፥4-6። እንግዲህ ሦስቱን አካላት ከግብራቸው የተነሣ በአሳባችን ስንለይ፥ በአስተርእዮ ግን በግብራቸው ሦስቱ አካላት እንደማይለያዩ መርሳት የለብንም።

4) በብሉይ ኪዳን የተገለጠ እግዚአብሔር ሦስት አካላት በአንድ አምላክ በመሆኑ ስለ ሦስትነቱ ብዙ ምልክቶችን ማግኘታችን አስገራሚ አይደለም። እኛም ብሉይ ኪዳንን በአዲስ ኪዳን ባለው ሥላሴያዊ አተረጓጐም እንመለከተዋለን። ሆኖም ስለ ሥላሴ ትምህርታችንን ለማረጋገጥ ቀጥታ አዲስ ኪዳን ውስጥ መግባት ይሻለናል። ይህን

ስናደርግ ብሉይ ኪዳንም ለአዲስ ኪዳን አገላለጥ ምቹ መንገድ የከፈተ መሆኑን መገንዘብ አለብን።

2. የሦስትነት አገላለጥ በአዲስ ኪዳን

ሀ) ሥላሴ በክርስቶስ ሕይወት ታሪክ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን ሲደመድም አሕዛብ «በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» እንዲጠመቁ በታላቁ ተልእኮ በማዘዙ፥ የእግዚአብሔርን አንድነትና የአካል ሦስትነት ገልጦ አረጋገጠ፤ ማቴ. 28፥19-20። «ስሞች» ሳይሆን «ስም» በማለቱ ሦስቱ አካላት ሦስት አማልክት አለመሆናቸውና ሦስቱ አካላት መለኮታቸውና ባሕርያቸው በአንድ አምላካዊ ህላዌ መገኘቱን መረዳት አያስቸግርም። ክርስቶስ ይህን ከመናገሩ ሦስት ዓመት በፊት ወልድ በሥጋ ሲጠመቅ፥ አብ፥ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» በማለቱና መንፈስ ቅዱስ በአካላዊ ቅርጽ እንደ ርግብ በክርስቶስ ላይ ወርዶ በመቀመጡ፥ ሦስቱ አካላት ሰውን በማዳን ሥራ የየራሳቸው ሥራ (ግብር) ሲኖራቸው ዓላማቸውና ፈቃዳቸው አንድ መሆኑን አሳዩ፤ ማቴ. 3፥16-17፤ ማር. 1፥10-11፤ ሉቃ. 3፥22፤ ዮሐ. 1፥32። እነዚህ ጥቅሶች ህላዌያዊ ሦስትነት (ONTOLOGICAL TRINITY) ማለት ሥላሴ በራሱ እንዳለ ይናገራሉ። ማቴዎስና ሉቃስ ስለ ኢየሱስ ታሪክና ትምህርት ሲጽፉ፥ ሦስቱን አካላት ይጠቅሳሉ። ይህም በኢየሱስ ጥምቀት የተገለጠው ሥላሴ የእምነታቸውና የኢየሱስ አሳብ ዐውድ መሆኑን ያሳያል፤ ለምሳሌ ማቴ. 12፥28፤ ሉቃ. 1፥35፤ 4፥17-19፤ 10፥21፤ 24፥48 ይመ.።

ለ) ሥላሴ በጳውሎስ መልእክታት

ሦስቱ አካላት የተጠቀሱባቸው ሌሎች ጥቅሶች ስለ ምግባራዊ ሦስትነት (ECONOMIC TRINITY) ማለት ሦስቱ አካላት ግብራቸውን (ሥራቸውን) ሲፈጽሙ ይገልጣሉ። ከእነዚህ መካከል ከሁሉ የበለጠ የታወቀው፥ «የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፥ የእግዚአብሔርም ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን» የሚለው ይሆናል፤ 2ቆሮ. 13፥14። እዚህ ላይ ክርስቶስ በቅደም ተከተሉ፥ ቀድሞ ይታያል። ከዚህ ጥቅስ የተነሣ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሦስቱ አንድ ላይ ከጻፈው ሦስት ነጥቦችን መመልከት ይገባናል ፦

1) እያንዳንዱ አካል ሁልጊዜ በአንድ ስም አይጠራም (8)። እዚህ ላይ አብ «እግዚአብሔር» ተብሎ ተጠርቷል። ብዙ ጊዜ ጳውሎስ በ«እግዚአብሔር» ሲጠቀም በኤፌሶን 3፥14-17 እና በገላ. 4፥6 በ«አብ» ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜ በ«ክርስቶስ» ሲጠቀም ደግሞ በሌሎች በተለይም በ«ልጅ» ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜም በ«መንፈስ»፥ በተወሰኑ ጥቅሶች ደግሞ በ«መንፈስ ቅዱስ» በማለት ሦስተኛውን አካል ይጠራል። ሐዋርያው በብዙ ጥቅሶች ሦስቱን ይገልጣል፤ ከእነዚህም መካከል በተለይ የታወቁት የሚከተሉት ይሆናሉ ፦ ሮም ም.8፤ 15፥15-16፤ 15፥30፤ 1ቆሮ. 12፥4-6፤ 2ቆሮ. 1፥21-22፤ 3፥3፤ 13፥14፤ ገላ. 4፥4-6፤ ኤፌ. 1፥3-14፤ 2፥18፤ 3፥14-17፤ 4፥4-6፤ ፊል. 3፥3፤ 2ተሰ. 2፥13-14።

2) በየጥቅሱ የተጠቀመበት የአካላት ቅደም ተከተል የተለያየ ነው (9)። የሦስቱ ስም ቅደም ተከተል በአማርኛ በትርጉም ወይም በሰዋስው ምክንያት ከግሪኩ ጋር ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ በ2ቆሮንቶስ 13፥14 ቅደም ተከተሉ ክርስቶስ፥ እግዚአብሔር፥ መንፈስ ቅዱስ የሚል ነው፤ ለዚህም በግሪኩ አጻጻፍ መሠረት አንድ ምክንያት ሊኖር ይችላል፤ ይኸውም ግሪኮች ስለ ሦስት ነገሮች ሲጽፉ ከሦስቱ በአንዱ

ላይ ትኵረት ለማድረግ ሲፈልጉ፥ የሚያተኵሩበትን በመጀመሪያ ጠቅሰው ሁለተኛውና ሦስተኛው የአንደኛውን አሳብ እንዲያንጸባርቁ በኋላ ያስቀምጧቸው ነበር። በዚህ አመለካከት በ2ቆሮንቶስ 13፥14 «የእግዚአብሔር ፍቅር» በክርስቶስ መገለጡንና «የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት» በክርስቶስ (ወይም ከክርስቶስ ጋር) መሆኑን ያሳያሉ፤ በዚህ አሳብ መሠረት የዚህ ጥቅስ ትኵረት በወልድ ግብር ላይ ነው።

3) የሦስቱ አካላት አጠቃቀስ ህላዌያዊውን ሦስትነት ሳይሆን በተለይ ምግባራዊውን ያብራራል። አስቀድመን እንዳተትነው እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጠው በተለይ በሥራው ነውና ሦስቱን አካላት በመጀመሪያ የምናውቃቸው በግብራቸው ነው። ክርስቶስ ሦስቱን የጠቀሰው በጥምቀት ምክንያት ነበረ፤ ማቴ. 28፥19-20። በሰው ደኅንነት የሦስቱ ግብር በጳውሎስ መልእክታትም ሆነ በሌሎች በብዙ ጥቅስ ቢገለጥም አንድ ዐይነት ነው፤ ይህንም እንደሚከተለው ተገልጦ እናገኘዋለን ፦

- እግዚአብሔር አብ የሚወስን፥ የሚያረጋግጥ፥ የሚፈርድና የሚሾም አካል ነው፤

- እግዚአብሔር ወልድ፥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኀኒት፥ አዳኝ፥ መሥዋዕት፥ ማስተስረያና የምእመናን ደኅንነት ዋስትና የሚሆን፥ እንደዚሁም ምእመናን እርሱን ይመስሉ ዘንድ እንደገና የሚፈጠሩበት አካል ነው፤

- መንፈስ ቅዱስ ሰውን የሚቀድስ ለአገልግሎትና ለምስክርነት የምእመናን ኀይልና ለሚመጣው የምእመናን ክብር መያዣ ዋስትና የሚሆን አካል ነው (10)። በዐጭሩ በሰው ደኅንነት አብ ያቅዳል፤ ወልድ ያደራጃል፤ መንፈስ ቅዱስ ይፈጽማል ማለት ይቻላል። ሆኖም አንዳንዶች በዚህ አባባል አይደሰቱም፤ ምክንያታቸውም የሦስቱ ግብር የሚፈጸመው ለየብቻቸው ሳይሆን በአንድነት በመሥራታቸው ነው የሚል ነው።

ሐ) ሥላሴ በሐዋርያው ጴጥሮስ ስብከትና መልእክት

መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ከወረደ በኋላ፥ ጴጥሮስ ክርስቶስ ከማረጉ በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ በሰጠው ሥላሴያዊ ተስፋ ቃል መሠረት (ሐ.ሥ. 1፥7-8)፥ «(ኢየሱስ) በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው» ብሎ በመንፈስ ቅዱስ አሰጣጥ የአብንና የወልድን ሥራ አብራራ፤ ሐ.ሥ. 2፥33። እዚህ ላይ ሉቃስ እንደ ሌሎች የወንጌል ጸሐፊዎች የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎትና የክርስቶስን ጥምቀት በመጥቀስ ታሪካቸውን በሥላሴያዊ ዐውድ እንደተረከው እናያለን፤ ሐ.ሥ. 1፥4-8። ጴጥሮስ መልእክቱን ሲጀምር ስለ ምርጦቹ የአብን አስቀድሞ መወሰን፥ የወልድን ደም መረጨትና የመንፈስ ቅዱስን መቀደስ ይገልጣል፤ 1ጴጥ. 1፥1-2 (በቀ.አ. እና በአ.መ.ት. ይመ.)።

መ) ሥላሴ በይሁዳ መልእክት

ይሁዳ፥ «በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ» በማለት የሦስቱን አካላት ግብር አስፈላጊነት በአማኙ ሕይወት ያሳያል (ቍ. 20-21)።

ሠ) ሥላሴ በሐዋርያው ዮሐንስ መጻሕፍት

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈላቸው ሰዎች፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንዲያምኑና አምነው በስሙ ሕይወት እንዲሆንላቸው ነው፤ 20፥31። ይህንም ሲያደርግ ኢየሱስ ከአብ ጋር አንድ መሆኑንና ከአብ እንደመጣ፥ ሥራውም በመንፈስ

ቅዱስ እንደሚፈጸም አሳየ። ሦስቱ አካላት ከኒቆዲሞስ ጋር በተደረገው ታዋቂ ንግግር (3፥3-16) ቢጠቀሱም፥ በተለይ በም. 14-16 በአንድነት ተጠቅሰው ይገኛሉ፤ እነርሱም :-

«እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ... የእውነት መንፈስ ነው» (14፥14-17)፤

«አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ» (14፥26)፥

«እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል ...» (15፥26)፤

«እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም ... እርሱ ዓለምን ይወቅሳል፤ ስለ ኀጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ ...» (16፥7-10)፥

«አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ ... መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ... አላቸው» (20፥21-23) የሚሉ ናቸው።

በዮሐንስ ራእይም ሦስቱ አካላት በልዩ ልዩ አጠራርና ምሳሌ በአንድነት ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ ዮሐንስ፥ «ካለውና ከነበረው ከሚመጣውም፥ በዙፋኑም ፊት ካሉት ከሰባቱ መናፍስት ከታመነውም ምስክር ከሙታንም በኵር የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን» ብሎ በመግቢያው በመጻፉ፥ ራእዩ የተመሠረተው በሥላሴያዊ ዐውድ ላይ መሆኑን ያመለክታል፤ ራእ. 1፥4-6።

በዮሐንስ ወንጌል ስለ ሥላሴ የተሰጠውን ትምህርት በሚከተለው ምዕራፍ በሰፊት እንመረምራለን። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ሦስቱን አካላት ብዙ ጊዜ በአንድነት በመጥቀሳቸው፥ ምሥጢረ ሥላሴ ለትምህርታቸው ዋና ዐውድ መሆኑን አይተናል። ጸሐፊዎቹ ከሦስቱ አካላት ሁለቱን ወይም አንዱን ብቻ በልዩ ልዩ ስፍራ ሲጠቅሱ፥ ከአሳባቸው በስተኋላ ሦስቱ እንዳሉ ግልጥ ነው። ብዙ ጊዜ እነዚህ ጥቅሶች «ትምህርተ ክርስቶስ» እና «ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» በተሰኙት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር ወልድና ስለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ትምህርት እንጠቀምባቸዋለን።

## ሐ) የትምህርተ ሥላሴ ጥናት መነሻ (11)

የሥላሴ ትምህርት፥ በአንድ አምላክ ሦስት አካላት አሉ፤ ሦስቱ አካላት በአንድ አምላክ ይገኛሉ የሚለው ነው። ይህን ትምህርት ስናጠና በአንዱ አምላክ ወይስ በሦስቱ አካላት መጀመር ይሻላል? በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ምእመናን በአንድ አምላክ ትምህርታቸውን ጀመሩ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ብዛት ወይም ሦስትነትም እንኳ እንዳለ በመጠኑ የተረዱ እንደሚመስለን አይተናል (ም. 25 ለ1)። ክርስቶስ አገልግሎቱን ሲጀምር፥ ቀስ በቀስ መሲሕና የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መሆኑና ስለ መንፈስ ቅዱስ አስተማረ። መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ ግን ሐዋርያት አንድ እውነተኛ አምላክ እንዳለ ሲያስተምሩ፥ ስለ ክርስቶስና ስለ መንፈስ ቅዱስ በግልጥ ማስተማራቸውን አይተናል። ስለ ሥላሴ በዝርዝር ባያስተምሩም የሦስቱን አካላት ሥራ እየገለጡ አድማጮቹ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሁሉ ተረድተው በሕይወታቸው ሕያው ውጤት እንዲኖራቸው አሳሰቡ። ስለ ሥላሴ ስናስተምር ዓላማችን የሐዋርያት ዓላማ መሆን አለበት፤ አብን፥ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን የምናውቃቸው በሥራቸው ነውና። በሦስቱ አካላት ብንጀምር ከአሳባችን በስተኋላ አንድ አምላክ ብቻ መኖሩን እንዳንዘነጋ መጠንቀቅ አለብን፤ አለበለዚያ በሦስት አማልክት ትምህርት ጉድጓድ ውስጥ ልንወድቅ

እንችላለን። በአንድ አምላክ ትምህርታችንን ብንጀምር ግን፣ እንደ አርዮስ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም የሆኑ አምላካዊ አካላት አለመሆናቸውን ወይም እንደ ሰባልዮስ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዳቸው አካልነት ሳይኖራቸው ሦስት የእግዚአብሔር አገላለጦች ብቻ መሆናቸውን ከማመን መጠንቀቅ ይኖርብናል። እነዚህ ስሕተቶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንዴት እንደተከሠቱ በም.27 እናትታለን።

በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንዳደረግነው ትምህርታችንን በሦስቱ አካላት ጀመርን፤ ምክንያቱም በዚህ ዘመን አካላዊነት ምን እንደሆነ እየተረሳ በመሄድ ላይ ይታያል።

## መ) በምሥጢረ ሥላሴ ጥናት የምንጠቀምባቸው ቃላት ትርጉም

ከዚህ በፊት ስለ እግዚአብሔር ስናብራራ በምንጠቀምባቸው ቃላት ላይ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባን አይተናል (ም. 21ሀ)። በተለይ ስለ ቅድስት ሥላሴ ስናጠና የሦስት ቃላትን አሳብ መረዳት ይኖርብናል።

### 1. የአካል ትርጉም

ሰውን በተመለከተ አካል ማለት ከሰው ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ያለው ሁሉ ነው ተብሏል። ሰው አካላዊ ነው ሲባል ማንነቱንና እኔነቱን ያሳስባል፤ አንድ ሰው ከሌላው የሚለየውም በአካላዊነቱ ነው። እኔ ሰው ነኝ፤ ነገር ግን ሰው መሆን ምን ማለት ነው ወይም ሰው የሚያሰኘው ምንድነው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ብዙ ሙከራ ተደርጓል፤ ሆኖም ሰው ምን እንደሆነ ለመወሰን ቢያስቸግርም፤ ማንም ሰው አካልነት እንዳለውና ምን ዐይነት ፍጡር መሆኑን ያውቃል። አንዳንዶች የሰው አካልነት የሚያስብ፣ የሚሰማውና የሚፈቅድ ችሎታ ያለው ነው የሚሉ አሉ። እውነት ነው፤ ሰው አስቦ ይሠራል፤ በሚያጋጥመው ሁሉ ስሜት ይሰማዋል፤ በሁለት ነገሮች መካከል የመምረጥ ፈቃዱን ያሳያል፤ ብዙ ጊዜም ፈቃዱ ግብረገባዊነቱን ይገልጣል። ሌሎች ደግሞ ሰው አካላዊነቱን የሚያሳየው ከሌሎች አካሄድና ጠባይ በመለየቱ፣ ለሌሎች ሥራ በመሥራቱ፣ ከሌሎች ጋር በመገናኘቱና አመክንዮታዊ አስተሳሰቡን በመግለጡ ነው ይላሉ። እነዚህ አራት መስፈርቶች በሰዎች ብቻ ሳይሆን በመላእክትም ይታያሉና እነርሱም አካላውያን ፍጡራን ናቸው። የአካልነት ምንጭም አካላዊው ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ነው። አካል፣ አካልነት፣ አካላዊና አካላዊነት PERSON, PERSON-HOOD, PERSONAL እና PERSONALITY የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት ሊተረጉሙ ይችላሉ።

የሰውና የእግዚአብሔር አካልነት አንድ አይደሉም፤ ሆኖም ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ፣ በእግዚአብሔርና በሰው አካልነት መካከል ብዙ ተመሳሳይነት ይኖራል። ከሰው በመነሣት በተመሳሳይነት በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን አካልነት ለመረዳት ስንፈልግ ሦስት ርምጃዎችን እንወስዳለን ፦

ሀ) ሰው ፍጡርና ኀጢአተኛ በመሆኑ በአካልነቱ ያለውን ማናቸውንም ዐይነት የጒድለት አሳብ ማስወገድ ያስፈልጋል። ሰው ፍጡር ከመሆኑ የተነሣ በአካልነቱ በሚታየው በማናቸውም ዐይነት ውሱንነት ፈንታ በእግዚአብሔር ዘንድ ምልአት እንዳለ መገንዘብ ተገቢ ነው። ለምሳሌ ሰው በዕውቀቱ፣ በኀይሉና በአንድ ስፍራ በመገኘቱ ውሱንነት፣ ዝቅተኛነት፣ የበታችነት ...ወዘተ የሚሰማው ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር አካልነት ላይ ግን ምልአት እንጂ ጒድለት የለም፤ እርሱ በሰላምና በአግባብ ሁሉን አስቦ እንደ ፈቃዱ ይፈጽማል።

እንደዚሁም ሰው ኀጢአተኛ በመሆኑ በአካልነቱ የሚታዩበት ማናቸውም ዐይነት የክፋት አሳብ፥ የሞት ፍርሀት፥ የጠባይ ለውጥ፥ የበደል ስሜት፥ የከንቱነት አስተሳሰብ ... ወዘተ በእግዚአብሔር አካልነት ፈጽሞ አይገኙም። በዚህ ፈንታ በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅና ቅድስና ይሰፍናሉ።

አንድ ሌላ ምሳሌ መስጠት እንችላለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በሰው አካል ውስጥ «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ»፤ ስለዚህ ሰው የሚወደውን ማድረግ እንደማይችል ጽፏል፤ ገላ. 5፥17። እግዚአብሔር ግን በባሕርዩ የሚጋጭ ነገር የለበትምና የሚወደውንና የሚፈልገውን ዐውቆ ያደርጋል፤ በእርሱ ዘንድ መከፋፈል የለም።

ለ) በሰው አካልነት የማይገኙ ብዙ ነገሮች በእግዚአብሔር አካልነት እንደሚኖሩ በአሳብ መገንዘብ ነው። የእግዚአብሔርን ስሞችና የባሕርዩ መገለጫዎች ስንመለከት፥ አካልነቱ ከሰው አካልነት እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን ያሳስባሉ። በምዕራፍ 22-24 ያጠናነው ሁሉ ይህን ያሳያል፤ በተለይም ሁሉን ቻይነቱና ልዕልናው ለአካልነቱና ለአካላዊነቱ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አላቸው።

ሐ) እነዚህን ሁለት ርምጃዎች ከወሰድን በኋላ በሰው አካልነት ያሉት የማሰብ፥ ስሜትን የመግለጥና የመፍቀድ ችሎታዎች በእግዚአብሔር ዘንድም እንዳሉ ማጤን እንችላለን። እንደዚሁም ሰው ከሌሎች ጋር እንዴት እንደሚኖር፥ ለሌሎች እንዴት እንደሚሠራ፥ ከሌሎች ጋር እንዴት እንደሚገናኝና አመክንዮታዊ አስተሳሰቡን እንዴት እንደሚገልጥ በማሰብ፥ የእግዚአብሔርን አካላዊነት ምን ያህል መረዳት እንደሚችል ማሰላሰል ይጠቅማል።

በአንዱ እግዚአብሔር ዘንድ ሦስት አካላት እንዳሉ በብዙ ጥቅሶች አይተናል። አካላዊነታቸው በዮሐንስ ወንጌል በተለይም በምዕራፍ 14-17 ይታያል። በእነዚያ ምዕራፎች ውስጥ የሦስቱ አካላት ምግባሮች፥ እርስ በርሳቸውም እንዴት እንደሚገናኙ ተገልጧል። አብ ወልድን ሲልክ፥ በአገልግሎቱ ይረዳዋልና ያጸናናዋል፤ መንፈስ ቅዱስንም ይልካል። ወልድ ወደ አብ ይጸልያል፤ አብን ያከብራል፤ ራሱን ለአብ ፈቃድ ያስገዛል፤ ወደ አብም ተመልሶ የቀደመ ክብሩን ይጐናጸፋል፤ እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስን ይልካል። መንፈስ ቅዱስ ከአብ ወጥቶ በወልድ ላይ ይኖራልና ይመሰክርለታል፤ በወልድ አማካይነት ወደ ዓለም ተልኮ ይሠራል፤ አብንም ይለምናል (ሮም 8፥26-27)። ስለ እነዚህ ድርጊቶች ቈየት ብለን በዝርዝር እናትታለን፤ ስለ ልመና (አማላጅነት) ማስታወሻ (12)ን ይመ.። በምእመናን ደኅንነት የሦስቱ አገልግሎት የተለያየ መሆኑን አይተናል (በዚህ ምዕራፍ ለ2 ለ3 ይመ.)።

ግንኙነታቸውን በይበልጥ ስንመረምር፥ ወልድ የአብ ውድ ልጅ ነው (ቆላ. 1፥13) «አንድያ» ልጅም ነው፤ ዮሐ. 3፥16። መልአክ ወይም ሰው ይህ ዐይነት ስፍራ አይኖረውም። ክርስቶስ የእግዚአብሔር (የአብ) አንድያ ልጅ (አንድ ብቻ የሆነ ልጅ)፥ የራሱ የባሕርይ ልጅ፥ ውድ ልጁ ነው። ዮሐንስ፥ «ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ» (1፥1) ሲል ለአብ ያለውን የልጁን ፍቅር ያብራራል። በዚህ ጥቅስ ላይ «በ... ዘንድ» ወይም «ከ... ጋር» (አ.መ.ት.) ተብሎ የተተረጐመው መስተዋድድ ወደ እግዚአብሔር (ወደ አብ) በጕጕት መመልከት የሚለውን አሳብ ይይዛል፤ ስለዚህ ሐረጉ ወልድ ከአብ ጋር መኖሩን ብቻ ሳይሆን ፊት ለፊት መተያየታቸውንም ያመለክታል። ስለዚህ ሰው ከሚያውቀውና ማሰብ ከሚችለው በላይ በአብና በወልድ መካከል አስደናቂ ፍቅር አለ።

በሰው አካልነት አመክንዮታዊ አስተሳሰብ አለ፤ በእግዚአብሔር ዘንድም የባሕርዩን መገለጫዎች በመረመርን ጊዜ (ም.23-24) ከሰው ይልቅ የእርሱ አሳብ፥ ዕቅድ፥ ዓላማ፥ ፈቃድና ስሜት ከፍ ያሉ መሆናቸውን በሚገባ ተገንዝበናል። አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም መለኮት ስለሚኖራቸውና የባሕርይ መገለጫዎች ሁሉ ስላሏቸው፥ አካልነታቸው ምሉእ ነው። በሰው አካልነት ጉድለት አለበት፤ ስለዚህ ከሰው ይልቅ እግዚአብሔር አካላዊ ነው ማለት ተገቢ ነው።

ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ስንነጋገር አካልን፥ አካልነትን፥ አካላዊንና አካላዊነትን በተመለከተ ሁለት ዐይነት አስተሳሰብ ሊኖረን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ አካላዊ ስንል በሰዎች መካከል የ«እኔ፥ አንተ፥ እርሱ» ግንኙነት እንዳለ እንመለከታለን። በሌላም ጊዜ አካላዊ ስንል ያ አካል የራሱ ህላዌ (መኖር፥ መሠረት፥ አቋም ...) እንዳለው እናስባለን። በሰዎች (እንደዚሁም በመላእክት) ዘንድ እያንዳንዱ ሰው የራሱ አካልና ህላዌ አለው፤ ሦስት ሰዎች ካሉ ሦስት አካላት አሉ፤ ሦስት ህላዌዎችም አሉ። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ህላዌው አንድ ብቻ ነው፤ ከሦስቱ አካላት እያንዳንዱ ህላዌ አለው፤ የሦስቱ አካላት ህላዌ ያው አንዱ የእግዚአብሔር ህላዌ ነው። እንዴት? ተብሎ ቢጠየቅም መልሱ ምሥጢር ነው የሚል ይሆናል። እንደዚሁም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መለኮት አላቸው፤ መለኮታቸውም ያው የአንዱ እግዚአብሔር መለኮት ነው። ባሕርይን በተመለከተም፥ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ባሕርይ አላቸው፤ ባሕርያቸው ግን የአንዱ እግዚአብሔር ባሕርይ ነው። በዚህም ምክንያት የሦስቱ አካላት የባሕርይ መገለጫዎች የአንዱ እግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫዎች ናቸው። በዚህ ምክንያት «በመለኮትና በባሕርይ አንድ» የሚለው የትምህርተ ሥላሴ ዐቢይ ነጥብ ሆኖ ትኩረት ይደረግበታል።

2. የአንድነት ትርጉም

አንድ፥ ሁለት፥ ሦስት ... ወዘተ ብለን እንቈጥራለን። አንድ ድንጋይ፥ ሁለት ድንጋዮች፥ ሦስት ድንጋዮች ... ወዘተ ማለት እንችላለን፤ ይህም የሒሳብ አንድነት ነው። ክርስቶስ፥ «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ. 10፥30) ሲል ሌላ ዐይነት አንድነት ነው፤ ይህን አንድነት ምሥጢራዊ አንድነት ብለን ልንጠራው እንችላለን። ባልና ሚስት «አንድ ሥጋ» ይሆናሉ (ዘፍ. 2፥24)፤ ይህም ምሥጢራዊ አንድነት ነው። እንግዲህ የሥላሴ አንድነት ሒሳባዊ ሳይሆን፥ ምሥጢራዊ አንድነት ነው።

በአንድ ክበብ ብዙ አባላት ሊገኙ ይችላሉ። አሳባቸው አንድ ላይሆን ይችላል፤ ብዙዎቹ ምናልባት ላይተዋወቁና ተገናኝተው የማያውቁ ይሆናሉ። አባሎች ከክበቡ ሊወጡ ይችላሉ፤ የተሳሰሩ አይደሉም። አባላቱ ሊቈጠሩ ይችላሉ፤ ከዚህ በላይ አንድነት አላቸው ማለት ያስቸግራል።

በአንድ ቡድን የሚጫወቱ የበለጠ አንድነት አላቸው፤ አንድ ግብ አላቸው፤ በቍጥር የተወሰኑ ናቸው፤ ይተዋወቃሉና ይገናኛሉ። ቡድን ምግባራዊውን ሦስትነት ሊመስል ይችላል፤ የተጫዋቾች ህልውና አንድ ባለመሆኑ ቡድን ህላዌያዊውን ሦስትነት አይመስልም።

በዕንቍላል ውስጥ አስኳል፥ ውሃና ቅርፊት አሉ፤ ዕንቍላል ያለ እነርሱ ዕንቍላል ሊባል አይችልም። ሦስቱ የዕንቍላል ክፍሎች እንጂ አንድ ወይም አንድ ዐይነት ህላዌ የላቸውም። እንግዲህ የሥላሴ አንድነት ምሥጢራዊ ቢሆንም ልዩ ነው፤ ሦስትነትን የሚገልጥ ትክክለኛ ምሳሌ አይገኝም፤ ሥላሴ ምሥጢር ነውና።

3. የሥላሴ ምሥጢር (13)

(12) አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ ወይም ክርስቶስ «ይለምናል» (ያማልዳል) በማለት በሰውኛ አገላለጥ የሰማያዊውን ድርጊት ይተረጉሙታል። በምድርና በሰማይ ላይ የሚከናወነው «አማላጅነት» ተግባር ለምእመናን ውጤቱ አንድ ቢሆንም፥ አማላጅነት አንድ ዐይነት እንደሆነ የሚያሳይ አይደለም። ይህን በጥናት ስድስት በሰፊው እንደምናትት ተስፋ እናደርጋለን።

(13) ይህ ክፍል በBERKHOF ገጽ 89F ላይ ከተጻፈው የተገኘ ነው።

# ምዕራፍ 26 - ትምህርተ ሥላሴ

ስለ ቅድስት ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱስ ወደሚሰጠው ትምህርት ከመግባታችን በፊት አምስት ነጥቦችን መገንዘብ ሊረዳን ይችላል ፦

1. መጽሐፍ ቅዱስ በአንዱ እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንዳሉ ያስተምራል። ይህም ትምህርት በፊተኛው ምዕራፍ እንዳየነው የሚመሠረተው በአንድ ጥቅስ ብቻ ሳይሆን በብዙ ጥቅሶች ላይ ነው። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች «ትምህርተ ሥላሴ» የተሰኘው ጥናት አልነበራቸውም፤ ነገር ግን የሦስቱን ሥራ በራሳቸው ሕይወት ስላወቁ የሦስቱ አካልነትና ምግባር ከአምልኮታቸው፥ ከጸሎታቸው፥ ከሕይወታቸውና ከአገልግሎታቸው ጋር የቀረበ ግንኙነት ያለው ዐውድ ነበረ።

2. በሦስቱ መካከል ፍጹም ፍቅር አለ። ፍቅር ካለ ወዳጅና ተወዳጅ አሉ፤ አንዳንዶች ፍጹም ፍቅር እንዲኖር ሦስተኛ አካል ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም እውነተኛ ወዳጅ ተወዳጁ ሌላ እንዲወድና በሌላ እንዲወደድ ይፈልጋል ይላሉ። ሌሎች ደግሞ እውነተኛ ፍቅር እንዲገኝ እያንዳንዱ አካል ለመውደድ ወይም ላለመውደድ ነጻነት እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ አለበለዚያ ግንኙነታቸው በፍቅር ሳይሆን በግዴታ የሚወሰን ይሆናል ይላሉ። እነዚህ አሳቦች ከፍልስፍና የሚገኙ ናቸው፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ልናረጋግጣቸው ባንችልም ለጊዜው ትክክለኛ ሊመስሉን ይችላሉ።

3. መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ መሆኑን ያስተምራል። ይህን ለማሳየት አንዳንዶች በእግዚአብሔር አብ ይጀምራሉ፤ እንደዚህ የሚያደርጉትም ሁሉ ከእርሱ ስለሚጀምር ነው። ሌሎች በእግዚአብሔር ወልድ ይጀምራሉ፤ ምክንያቱም ወልድ ለእግዚአብሔር መንገዱ ነውና። የተወሰኑት ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይጀምራሉ፤ ምክንያቱም እርሱ ለሰው አስተርእዮን የሚገልጥ ነውና። እኛ ግን በተናጠል ሳይሆን በሦስቱ አካላት በአንድነት እንጀምራለን፤ ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን ዘመን ክርስቲያን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃል፤ ሲያምንም ወደ ሥላሴ ኅብረት ገብቶ ከሦስቱ ጋር ይገናኛል።

4. አማኞች ሦስቱን አካላት በሥራቸው ያውቋቸዋል። በፍጥረት እግዚአብሔር፥ የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ልዩ ሥራዎች በመጠኑ ቢታዩም፥ በተለይ በደኅንነት ሥራ የሦስቱ ድርሻ በግልጽ ይንጸባረቃል። ሦስቱ በአዲስ ኪዳን በአንድነት ሲጠቀሱ፥ ዋናው ትምህርት በምግባራቸው ላይ የሚያተኩር መሆኑን አይተናል (ይህም ምግባራዊ ሦስትነት ተብሏል)። ሆኖም በሦስቱ አካላት መካከል የእርስ በርስ ግንኙነት እንዳለ ግልጥ ነው፤ ይህ ግንኙነት የተገለጠው በተለይ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 14-16 ነው (ይህም ህላዌያዊ ሦስትነት ተብሏል)።

5. ቅድስት ሥላሴ ምሥጢር ነው። ሆኖም ሦስቱን አካላት በመጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት ስለ ሥላሴ ልዩ ልዩ ትምህርት እንዳለ ማተት እንችላለን። ይህ ትምህርት ፍጹም ወይም ሙሉ አይደለም። ምሥጢር አለ፤ ብዙ ነገር ለሰው አልተገለጠም። ሰው በዚህ ዓለም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖር ያልተገለጡ ነገሮች ሁሉ አያስፈልጉትም፤ ሁሉ ቢገለጡም ኖሮ ሊያስተውላቸው የሚችል አይመስልም ነበር። ስለ ሦስቱ አካላት በአንዱ አምላክ የተገለጠውን በአራት አርእስት ለማጠቃለል እንሞክራለን።

## ሀ) የሦስቱ አካላት መለኮት

እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ሦስትም ነው ማለት ትክክለኛ ነው። ይህን ለመመርመር ሦስቱን አንድ በአንድ እንመለከታለን።

1. እግዚአብሔር አብ ፍጹም አምላክ ነው

ሐዋርያት ለአንባቢዎቻቸው ሰላምታ ሲያቀርቡ፥ ብዙ ጊዜ «እግዚአብሔር አብ» ብለው ጽፈዋል፤ ገላ. 1፥1፤ 1ተሰ. 1፥1፤ 2ጢሞ. 1፥2፤ ቲቶ 1፥4፤ 1ጴጥ. 1፥1-2፤ 2ዮሐ. 3፤ ያዕ. 1፥27። እግዚአብሔር አብ ወይም አባት ተብሎ ሲጠራ፥ የእስራኤል ሕዝብ አምላክ መሆኑን፥ የዓለም ፈጣሪ መሆኑን፥ የወልድ (የክርስቶስ) የባሕርይ አባት፥ የምእመናን ደግሞ የጸጋ አባት መሆኑን ሊያመለክት እንደሚችል በም. 22 ለ3 ገልጠናል። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «አንድ እግዚአብሔር አለ» (1ጢሞ. 2፥5) እና «አንድ አምላክ አብ አለን» (1ቆሮ. 8፥6) በማለቱ፥ እንደዚሁም ጌታችን፥ «አባት ሆይ ... እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ ...» ብሎ በመጸለዩ (ዮሐ. 17፥1-3) አብ ፍጹም አምላክ መሆኑ፥ ከእርሱም በፊት ሆነ ከእርሱ በላይ ማንም እንደሌለ ግልጥ ነው።

2. እግዚአብሔር ወልድ ፍጹም አምላክ ነው

«ትምህርተ ክርስቶስ» በሚለው መጽሐፍ በብዙ መንገድ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑ በዝርዝር ይገለጣል (1)። እዚህ ላይ ግን ክርስቶስ ራሱና አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ፍጹም አምላክ መሆኑን እንደመሰከሩ እናሳያለን።

በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ፥ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ... ቃልም ሥጋ ሆነ ... በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» ብሎ ዮሐንስ ጽፏል፤ ዮሐ. 1፥1:14:18። በዚህ አገላለጥ «ቃል» እግዚአብሔር ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው፤ ስለዚህ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር፥ «አባቴ» በማለት የእግዚአብሔር አብ ልጅ መሆኑን እንዳወቀ አሳይቷል፤ በዚህም እንደ አይሁድ አስተሳሰብ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከሉን አመለከተ፤ 5፥17-18፤ 8፥54። ኢየሱስ የአይሁድን የተሳሳተ አመለካከት በቀጥታ ለማረም አልሞከረም፤ በዚህ ፈንታ አብ የሚያደርገውን ወልድ እንደሚያደርግ (5፥19)፥ አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ፥ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን እንደሚሰጥ (5፥21)፥ አብን የሚያከብሩ ሁሉ ወልድን ማክበር እንደሚገባቸው አስተማረ። ወልድን ባያከብሩ ግን አብንም እንደማያከብሩት አስገነዘባቸው፤ 5፥21-23። ከሙታን የተነሣው ክርስቶስ፥ «እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፥ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም ዐርጋለሁ» ብሎ በመግደላዊት ማርያም አማካይነት ለተከታዮቹ መልእክት በመላኩ፥ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያላቸው ግንኙነት ልዩ ግንኙነት መሆኑን አሳየ፤ 20፥17። የእነርሱ ልጅነትና የእርሱ ልጅነት የተለያዩ ናቸው፤ በመለኮት በኩልም ዝምድናቸው አንድ አልነበረም። አንዳንዶች፥ ሐዋርያት «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ...» ብለው አብን የጠሩት፥ ክርስቶስን እንደ ፍጹም አምላክ አይቈጥሩትም ነበርን? ብለው ይጠይቃሉ፤ 1ጴጥ. 1፥3-5፤ ኤፌ. 1፥3። እዚህ ላይ ታላቅ ምሥጢር መኖሩ አይካድም። ሆኖም ክርስቶስ ራሱ «አምላኬ» ብሎ ስለተናገረ ሐዋርያት ትክክለኞች መሆናቸውን እናስተውላለን። በሌላ በኩል ወልድ ሰው በመሆኑ በወንጌል ታሪክ ብዙ ጊዜ እንደ ሰው ሲጸልይ እናገኘዋለንና ሰው ለአምላኩ ይጸልያል፤ ይህም አብና ወልድ ልዩ አካላት መሆናቸውን ያሳያል። ደግሞም፥ «እኔና አብ አንድ ነን» በማለቱ ሁለት አካላት ሲሆኑ፥

አንድነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ዮሐ. 10፥30። ክርስቶስ አምላኬ ቢልም እርሱ ራሱ አምላክ ነው፤ ሆኖም አምላክ ብቻ አልነበረም፤ ትስብእቱ ደግሞ ነበረና፤ ይህንም «ምሥጢረ ሥጋዌ» በሚለው ትምህርት እንመረምራለን። ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ዐውቆ «ጌታዬ፤ አምላኬም!» የሚለውን የቶማስን አምልኮት ሲቀበል፥ ስለ አለማመኑ እንጂ ስለ ተናገረው የአምልኮት ቃል አልወቀሰውም፤ 20፥28። ዮሐንስ ይህን ሁሉ የጻፈው ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፤ 20፥31።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አንዳንድ ወገኖች ወልድ አምላክ ቢባልም ከአብ የሚያንስ እንደሆነ ቈጠሩት። ሆኖም ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው ጥቅሶች ወደዚህ አሳብ ሊያመራ የሚችል አንድም ፍንጭ አይገኝም። ደግሞም አብና ወልድ ዓለም ሳይፈጠር በአንድነት ነበሩ (ዮሐ. 17፥5:24)፤ ወልድ አንድያ ልጁ ነው (3፥16) እና አብ ልጁን ይወዳል፤ 5፥20። የክርስቶስ ፍጹም አምላክነት በሐዋርያት ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተደግፏል። «ክርስቶስ በሥጋ መጣ፤ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው» የሚለው በልዕልናውና በዘለዓለማዊነቱ ላይ ያተኵራል፤ ሮም 9፥5። «እርሱ (ክርስቶስ) በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፥ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊተወው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም» የሚለው የወልድና የእግዚአብሔር አብ ባሕርይ አንድ እንደሆነና በመለኮት ወልድ ከአብ ጋር እኩል መሆኑን ያሳያል፤ ፊል. 2፥6 አ.መ.ት.። የዕብራውያን ጸሐፊ፥ «እርሱ (ወልድ) የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ» መሆኑን ከመሰከረ በኋላ ወልድን «አምላክ ሆይ፥ ...» ብሎ ይጠራዋል፤ ዕብ. 1፥3:8 አ.መ.ት.። ሐዋርያው ጴጥሮስም፥ «በአምላካችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ...» ብሎ ሰላምታውን በማቅረብ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና አዳኝነት አዛምዶ ይገልጠዋል፤ 2ጴጥ. 1፥1። አንድ ሰው ስለ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነት ቢጠራጠር፥ «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል» ከሚለው ወልድ ከአብ ያነሰ አለመሆኑን ማስተዋል ይገባዋል፤ ቆላ. 2፥9። የወልድ ፍጹም አምላክነት ከምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በዚህ ርእስ ሥር በሰፊው እንመረምረዋለን። አንዳንድ ጥቅሶች ወልድ ከአብ እንደሚያንስ ወይም አንድ ዐይነት የዝቅተኛነት ደረጃ እንዳለው የሚገልጡ ሊመስሉን ይችላሉ፤ ሆኖም እነዚህ ጥቅሶች ከማዳን ሥራ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ህላዌያዊውን ምስትንነት ሳይሆን ምግባራዊውን የሚያመለክቱ ናቸው። ምግባራዊው ምስትንነት ህላዌያዊውን አይገልጥም? ተብሎ ቢጠየቅም፥ መልሱ እነዚህ ጥቅሶች የወልድን ህላዌ፥ መለኮትና ባሕርይ ሳይሆን የግል አካላዊነቱን ሊያመለክቱ ይችላሉ የሚል ይሆናል። አካልነቱን ከዚህ በታች እንመለከተዋለን።

አንዳንዶች አብንና ወልድን እንደ ሁለት አካላት ሳይሆን ሁለት ገጸ ባሕርይን ወክሎ እንደሚቀርብ ተዋናይ አድርገው ይመለከቷቸዋል። ክርስቶስ ግን «እኔና አብ አንድ ነን» እንጂ «እኔና አብ አንድ ነኝ» አላለም፤ ዮሐ. 10፥30። አብና ወልድ አንድ አካል ከሆኑ ክርስቶስ ሲጸልይ ለራሱ ይናገር ነበርን? ብለን መጠየቅ እንችላለን። ደግሞም ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ከአብ እንደመጣና ወደ አብ እንደሚመለስ የተናገረው፥ ሁለት አካላት ባይሆኑ ምን ትርጕም ይሰጣል? የሚል ጥያቄ ያስነሣል፤ ዮሐ. 4፥34፤ 5፥24:37:43፤ 6፥38፤ 7፥28-29:33፤ 8፥14:16-18:21:23:26፤ 14፥28፤ 16፥28፤ 17፥4-5። በምድርም ሆነ በሰማይ አሁን ለሕዝቡ ስለሚለምን ከእርሱ ውጭ ሌላ የሚለመን መኖሩ ግልጥ ነው፤ እርሱም አብ ነው፤ ሉቃ. 22፥32፤ ዮሐ. 14፥15-16፤ ሮም 8፥34፤ ዕብ. 7፥25፤ ስለ ልመና (አማላጅነት) የም. 25

ማስታወሻ 12 ይመ.። ከዚህም ሌላ ሦስቱ አካላት በአንድነት ሲጠቀሱ፥ አብና ወልድ ሁለት አካላት መሆናቸው ይታያል፤ ም.25 ይመ.

3. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው

እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ዮሐ. 4፥24። ብዙ ጊዜ ብሉይ ኪዳን ከኦሪት ዘፍጥረት 1፥2 ጀምሮ ስለ «የእግዚአብሔር መንፈስ» ይናገራል። በብሉይ ኪዳን «የእግዚአብሔር መንፈስ» ሲል አካላዊ መንፈስ መሆኑ ወይም እንደ ፀሐይ ሙቀት ከእግዚአብሔር የሚወጣ ኀይል መሆኑ ግልጥ ባይሆንም፥ አዲስ ኪዳን «መንፈስ ቅዱስ»፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ» እና «የክርስቶስ መንፈስ» (ማቴ. 3፥11፤ ሮም 8፥9) ስለሚል፥ ስለ አካላዊው መንፈስ መናገሩ እሙን ነው። በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ ሲል አካላዊ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን እንደሚያመለክት ያምናሉ። «ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» በሚለው መጽሐፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ በሰፊው ለመጻፍ አሳብ አለን፤ ሆኖም እዚህ ላይ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ መሆኑንና ፍጹም አምላክ መሆኑን በዐጭሩ እንገልጣለን።

መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ቻይና አካላዊ መንፈስ መሆኑን በዐጭሩ ለማሳየት እንችላለን (2) :-

ሀ) በታላቁ ተልእኮ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት ስሙ በመቈጠሩ (ማቴ. 28፥19-20)፥

ለ) እንደ ክርስቶስ ያለ «ሌላ አጽናኝ» በመሆኑ (ዮሐ. 14፥15-16)፥

ሐ) ከአብ የወጣና የተላከ በመሆኑ (ዮሐ. 15፥26፤ ሐ.ሥ. 2፥33)፥

መ) በመናገሩ (ዮሐ. 16፥13-14፤ ሐ.ሥ. 1፥16፤ 8፥29፤ 10፥19፤ 11፥12፤ 13፥2፤ 28፥25)፥ በማስተማሩ (ዮሐ. 14፥26)፥ በመመስከሩ (ዮሐ. 15፥26)፥ በመፍቀዱና ባለመፍቀዱ (ሐ.ሥ. 16፥7፤ 1ቆሮ. 12፥11)፥ በማማለዱ (ሮም 8፥27) እና የመሳሰሉትን አካላዊ ድርጊቶች በመፈጸሙ፥

ሠ) ሰዎች ለእርሱ ዋሽተው በመናገራቸውና እርሱን በማሳዘናቸው (ሐ.ሥ. 5፥3:9፤ ኤፌ. 4፥30)፥

ረ) መንፈስ ቅዱስ ከኀይሉ ተለይቶ በልዩ ልዩ ጥቅሶች በመገለጡ (ሉቃ. 1፥35፤ 4፥14፤ ሐ.ሥ. 10፥38፤ ሮም 15፥13፤ 1ቆሮ. 2፥14-15) ነው።

መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ የምናውቀው :-

ሀ) ከአብና ከወልድ ጋር በብዙ ጥቅሶች በተለይም በማቴዎስ 28፥19-20 በመጠቀሱ፥

ለ) ከአብ የወጣና የተላከ በመሆኑ (ዮሐ. 15፥26፤ ሐ.ሥ. 2፥33)፥

ሐ) የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገርና አሳብ በመመርመሩና በማወቁ (1ቆሮ. 2፥10-11)፥

መ) መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ተብሎ በመጠራቱ (ሐ.ሥ. 5፥3:4)፥

ሠ) የክርስቶስ መንፈስ በመሆኑ (ሮም 8፥9፤ 2ቆሮ. 3፥17) ነው።

ከዚህ በላይ ከተጻፈው ሦስቱ አካላት አንድ ፍጹም አምላክ መሆናቸውን፥ እያንዳንዱ አካል የእግዚአብሔር ህላዌና ባሕርይ ሁሉ እንዳለው፥ በራሱም ፍጹም የሆነ ከሃሊነት ያለው አምላክ መሆኑን፥ መለኮቱን ከራሱ እንጂ ከሌላ አለመቀበሉን እናስተውላለን። ይህ በተለይ ከግሪክ ቋንቋ በተገኘው AUTOTHEOS በሚለው ቃል

ይታወቃል። ከዚህም መረዳት የምንችለው የእግዚአብሔር አካላዊነት ከሦስቱ አካላት የተነጣ የሚታይ መሆኑን ነው፤ ከሦስቱ አካላት ሌላ አካላዊነት የለውም።

ሦስቱ አካላት እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚገናኙና የሦስቱ አካላዊነት እንዴት እንደሆነ ቀጥሎ እንመለከታለን።

## ለ) የሦስቱ አካላት አንድነት

አንድነታቸው በብዙ በኩል ይታያል፤ ለምሳሌ :-

- ሦስቱ አምላክ ተብለዋል (ሀ ይመ.)።

- ሦስቱ ከዘለዓለም ናቸው፤ አብ ከዘለዓለም (ሮም 16፥25-26)፥ ወልድ ከዘለዓለም (ራእ. 22፥13:16)፥ መንፈስ ቅዱስ ከዘለዓለም (ዕብ. 9፥14) ናቸው።

- ሦስቱ ቅዱስ ናቸው፤ አብ ቅዱስ ነው (ኢሳ. 6፥3)፥ ወልድ ቅዱስ ነው (ሐ.ሥ. 3፥14)፥ መንፈስ ቅዱስ ቅዱስ ነው፤ ማቴ. 12፥27-28።

- ሦስቱ ሁሉን ያውቃሉ፤ አብ ሁሉን አስቀድሞ ያውቃል (ሮም 8፥29)፥ ወልድ ሁሉን ያውቃል (ዮሐ. 21፥17)፥ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ያውቃል፤ 1ቆሮ. 2፥10-11።

- ሦስቱ እውነት ናቸው፤ አብ እውነት ነው (ዮሐ. 7፥28)፥ ወልድ እውነት ነው (ዮሐ. 14፥6)፥ መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው፤ ዮሐ. 16፥13።

- ሦስቱ ይፈጥራሉ፤ አብ ይፈጥራል (ዘፍ. 1፥1)፤ ወልድ ይፈጥራል (ቆላ. 1፥16-17)፤ መንፈስ ቅዱስ ይፈጥራል፤ ኢዮብ 33፥4።

- ሦስቱ በስፍራ አይወሰኑም፤ በሁሉም ዘንድ ይገኛሉ፤ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ይሞላል (ኤር. 23፥24)፥ ወልድ የትም ዘንድ ይገኛል (ማቴ. 18፥20)፥ ሰው የትም ቢሄድ ከመንፈስ ቅዱስ አያመልጥም፤ መዝ. 139፥7።

- ሦስቱ ሕይወትን ይሰጣሉ፤ አብ የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣል (ሮም 6፥23)፥ ወልድ የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣል (ዮሐ. 10፥28)፥ መንፈስ ቅዱስ የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣል፤ ገላ. 6፥8።

- ሦስቱ በአማኞች ይኖራሉ፤ አብ በአማኞች ይኖራል (2ቆሮ. 6፥16)፥ ወልድ በአማኞች ይኖራል (ኤፌ. 3፥16-17)፥ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ይኖራል፤ 1ቆሮ. 3፥16።

- ሦስቱ ክርስቶስን ከሙታን በማስነሣት ተባበሩ፤ እግዚአብሔር ኢየሱስን አነሣ (ሐ.ሥ. 2፥24)፥ ኢየሱስ ራሱን አነሣ (ዮሐ. 2፥19)፥ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን አነሣ፤ ሮም 8፥11።

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የትምህርት ዝርዝር ለማስረዘም አዳጋች አይደለም፤ ሆኖም የሦስቱን አካላት አንድነት በፈቃድ፥ በባሕርይና በህላዌ ላይ ተመርኵዘን ማየት በቂ ሊሆን ይችላል።

### 1. የሦስቱ አካላት ፈቃድ አንድነት

ሦስቱ በፍጥረት፥ በመግቦት፥ በደኅንነትና በሌላም ሥራ ሲሳተፉ አንድ ፈቃድ አንድ ዓላማና አንድ ግብ አላቸው። በአንድ ሥራ ያላቸው ሚና የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ በዚህ ምክንያት በአንድ ሥራ ላይ ከሦስቱ አንዱ ቀድሞ ወይም ለየት ብሎ ይታያል (ም. 25 ለ2 ለ3 ይመ.)። ለምሳሌ በቀራንዮ መስቀል ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞተ። ታሪኩ

በተለይ ስለ እርሱ የሚናገር ቢሆንም አብና መንፈስ ቅዱስም አብረው አሉበት። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ፥ «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»፤ «አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ ዐደራ እሰጣለሁ» ብሎ በመጮኹ የአብን መገኘት ያሳያል፤ ሉቃ. 23፥34:46። «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?» ብሎ መከራን በተቀበለ ጊዜ ሲጮኽ እንኳ በሕማማቱ የአብን መገኘት ያሳያል። የዓለምን ኀጢአት ተሸክሞ ከቅዱስ አባቱ በኀጢአት ምክንያት መለየቱ ተሰማው እንጂ የአብን አለመገኘት አያሳይም፤ አለበለዚያ ወደ እርሱ አይጮኽም ነበርና፤ ማቴ. 27፥46። እንደዚሁም «በዘለዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ» (ዕብ. 9፥14) የሚለው ቃል፥ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ሲያቀርብ አብሮ መሳተፉን ያሳያል።

በትያትር ሥራ ሦስት ሦስት ተዋናዮች ሆነው ተውኔት ሲያቀርቡ፥ አንዳንድ ጊዜ ሦስቱም ይታያሉ፤ በሌላ ጊዜ ግን አንዱ ወደፊት ሆኖ ሁለቱ በስተኋላው ስለሚሆኑ አይታዩም፤ ነገር ግን ባይታዩም እንኳ እንዳሉ ይታወቃል። ይህ ምናልባት ለሦስቱ አካላት አሠራር በመጠኑ ምሳሌ ሊሆነልን ይችላል።

«የአንድ አምላክ አንድነት ምሥጢራዊነት አለው» ብለን ከዚህ በላይ እንደገለጥነው ሁሉ (ም. 25 ሀ2)፥ የእግዚአብሔር ፈቃድም ምሥጢራዊነት አለው። አብ ይፈቅዳል፤ ወልድ ይፈቅዳል፤ መንፈስ ቅዱስ ይፈቅዳል፤ ፈቃዳቸውም አንድ ነው፤ ምክንያቱም የአንዱ እግዚአብሔር ፈቃድ ነውና። ፈቃዳቸውም በሥራ ላይ ይገለጣል። የሦስቱ ፈቃድ በተለይ ሰውን በማዳን ላይ በአንድነት ሲሠራ ይታያል።

እግዚአብሔር አብ በምግባራዊ ሦስትነት «ዐቃጅ» እንደመሆኑ መጠን፥ «እንደፈቃዱ ምክር ሁሉን» ስለሚሠራ አማኞችን በክርስቶስ መረጣቸው፤ ወሰናቸውና በሰማያዊ ስፍራ ባረካቸው፤ ኤፌ. 1፥3:4:5:6:11። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በምግባራዊ ሦስትነት «አድራጊ» (ወይም «አቅራቢ») እንደመሆኑ መጠን፥ ስለ ሕማማቱ ሲናገር፥ «ነፍሴን ስለ በጎች አኖራለሁ ... ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞ ላነሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ» ብሎ መሰከረ፤ ዮሐ. 10፥15-18። በኋላም በጌቴሴማኒ፥ «አባቴ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን» በማለቱ በእርሱና በአብ መካከል የፈቃድ ልዩነት ያለ ሊመስለን ይችላል፤ ማቴ. 26፥39። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን መገንዘብ አለብን፤ መጀመሪያ እግዚአብሔር ወልድ ይህን የጸለየው በሰማይ ሳይሆን ሥጋን ከነሣ በኋላ በምድር ላይ ነው፤ ሁለተኛም በመስቀል ላይ ስለሚደርስበት «እጅግ ተጨንቆ» ላቡ እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ቢፈስም (ሉቃ. 22፥44)፥ ወዲያው የራሱ ፈቃድ የአባቱን እንዲከተል አደረገ። የአብና የወልድ ፈቃድ አንድነት ይታያል፤ ሆኖም በክርስቶስ ፈቃድ ምሥጢር እንዳለበት መካድ አንችልም፤ ይህንም «ምሥጢረ ሥጋዌ» በሚለው ትምህርት በዝርዝር ለማተት እንሞክራለን። መንፈስ ቅዱስም በምግባራዊ ሦስትነት «ፈጻሚ» እንደ መሆኑ መጠን፥ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጦታዎችን «እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል»፤ 1ቆሮ. 12፥11።

2. የሦስቱ አካላት ባሕርይ አንድነት

ባሕርይ አንድ ወገን የሆኑ የጋራ ወገንነታቸው (የጋራ አኳኋናቸውና ተመሳሳይነታቸው) ማለት ነው። ሰው በግለ ሰብእነቱ የተለያየ ሲሆን፥ ሁሉም ሰው የመሆን ባሕርይ ተሳታፊ ነው። የቅድስት ሥላሴ አካላትም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስት ሲሆኑ፥ አንድ ለሆነ የአምላክነት (የመለኮት) ባሕርይ ተሳታፊዎች ናቸው፤

እግዚአብሔር የባሕርይ አምላክ ይባላልና። የእግዚአብሔርን የባሕርይ መገለጫዎች በምዕራፍ 22-24 መርምረናል። ሆኖም የሦስቱ አካላት የባሕርይ አንድነትና የሦስት ሰዎች ባሕርይ አንድነት አንድ ዐይነት አይደለም። ምክንያቱም ሦስቱ ሰዎች ለየብቻቸው ሊኖሩ ይችላሉ፤ አንዱ ቢሞትም የሁለቱ ባሕርይ አይለወጥም። ህልውናቸው እንደ ቀድሞው ሆኖ ይቆያል። ሦስቱ የመለኮት አካላት ግን በአንድነት ይኖራሉ፤ አይለያዩም፤ አይለዋወጡም፤ አንድ ህልውና አላቸው።

ባሕርይን በተመለከተ በተለይ የወልድ ባሕርይ ምን እንደሚመስል በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብዙ ጥያቄ ተነሥቷል፤ ይህን አሳብ በተለይ በምዕራፍ 27 በስፋት እንመለከተዋለን። ጥያቄው የአብና የወልድ ባሕርይ አንድ ነው ወይስ ተመሳሳይ? የሚል ነው። ከብዙ ክርክር በኋላ ቤተ ክርስቲያን የወልድ ባሕርይ "HOMOIOUSIOS" (ተመሳሳይ ባሕርይ) ሳይሆን "HOMOOUSIOS" (አንድ ባሕርይ) በሚለው የግሪክ ቃል የጸና መሆኑን ወሰነች። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት የተደገገ ውሳኔ ነው፤ ድንጋጌውም በየዘመኑ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ተቀባይነትን አግኝቶ ጸድቋል።

3. የሦስቱ አካላት ህላዌ አንድነት

ህላዌ መኖር ማለት ነው። «ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት» ከተመሳሳይ የግእዝ ግሥ የሚገኘውን ተመሳሳይ ቃል ማለት ህልውናን «መኖር፥ አለመለወጥ በባሕርይ ጸንቶ መኖር ለእግዚአብሔር በጌትነቱ ዘመን፥ ዓመት ሳይቆጠርለት ጠንቶ መኖር» ይለዋል። ህልውና «እግዚአብሔር አለ» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ይገልጣል። ባሕርይ የሚለው ቃል ከህላዌ ጋር የተያያዘ ቃል ነው። እግዚአብሔርን በተመለከተ ህላዌ መኖሩን፥ መገኘቱን፥ አኳኋን ያለውንም ያመለክታል፤ ባሕርይም በራሱ እንዴት እንደሚኖርና ከፍጥረቱ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ያመለክታል፤ የባሕርዩም መገለጫዎች ባሕርዩ እንዴት እንደሆነ ያሳያሉ (ም. 22-24 ይመ.)።

ሦስቱ አካላት በአንድ ህላዌ ይኖራሉ። የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ህላዌ አንድ ነው። የአብ ህላዌ፥ የወልድ ህላዌ፥ የመንፈስ ቅዱስ ህላዌ ያው የአንዱ የእግዚአብሔር ህላዌ ነው። ስለ ሦስት ሰዎች ብናስብ ግን ሦስት ህላዌዎች አሉ፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ህላዌ አለው።

ግሪካውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ አንድ ነገር መኖር ሲናገሩ "HYPOSTASIS" በሚለው ቃል ይጠቀሙ ነበር። አንድ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን አመኑ፤ ሆኖም አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአንድ HYPOSTASIS እንዴት በአንድነት እንደሚገናኙ ብዙ ክርክር ነበረ። ክርክራቸውን በምዕራፍ 27 እናትታለን። ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ምሥጢር አለና በሚከተሉት ክፍሎች በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን ለማየት እንሞክራለን።

በዚህ ክፍል የሦስቱን አካላት አንድነት አትተናል። አንድነትን በህላዌ፥ በባሕርይና በፈቃድ አይተናል። ምንም እንኳ አምላክነትና መለኮት የተሰኙት ቃላት እጅግ የተቀራረበ ትርጉም ቢኖራቸውም፥ ያላቸውን መጠነኛ ልዩነት ከዚህ ቀጥሎ ከተገለጸው መረዳት ይቻላል። አንድነት በመለኮት አለ፤ ይህም ቃል ህላዌንና ባሕርይን ሊያጠቃልል ይችላል። አንድነት በአምላክነት አለ፤ ይህም ቃል ባሕርይንና የባሕርይ መገለጫዎችን ማጠቃለል ይችላል። ይህ አንድነት ምሥጢራዊ አንድነት መሆኑን አይተናል።

## ሐ) የሦስቱ አካላት ልዩነት

ሦስቱ አካላት በህልውና፥ በባሕርይ፥ በፈቃድ፥ በመለኮትና በአምላክነት አንድ መሆናቸውን አይተናል። ሆኖም ይህ አንድነት ምሥጢራዊነት ያለው እንደሆነ አጢነናል። ሦስቱ አካላት የተለያዩም ናቸው፤ ይህ ልዩነት የሚታየው በስሞቻቸው፥ በምግባራቸውና በአካላዊነታቸው ነው። ከዚህ በፊት የያንዳንዳቸውን ምግባር ጠቅሰናል፤ ለወደፊትም ይህ አሳብ በ«ትምህርተ ፍጥረት»፥ በ«ትምህርተ ግብረ ክርስቶስ» እና በ«ትምህርተ ድኅነት» በዝርዝር ይጠናል።

የሦስቱ አካላት አካላዊነት በምግባራቸው ይታያል፤ ህላዌያዊ ሦስትነታቸውም በስሞቻቸው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ በልዩ ልዩ ጥቅሶች በተለይም በዮሐንስ ወንጌል ይገለጣል።

### 1. የአብ አካላዊነት

የአብ አካላዊነት አባትነት ነው። አብን በተመለከተ የወልድ አካላዊነት ልጅነት ነው። አብና ወልድ አብ-ወልድ በሚል የግንኙነት አገላለጽ ከዘለዓለም ኑሯል። አብ ወደ ወልድነት (ልጅነት)፥ ወልድ ወደ አባትነት ተሸጋግረው ሚናዎቻቸውን አይለውጡም፤ ሁለቱም የራሳቸውን አካላዊነት አይቀይሩም። ይህ ግንኙነት ከመጀመሪያ ነበረ፤ ሆኖም ክርስቶስ፥ «አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቷልና» ብሏል፤ ዮሐ. 5፥26። በወንጌል ታሪክ ወልድ ሕይወት እንዳለው እናያለን፤ እንደ ፈቃዱ ሕይወቱን ማኖርና ማንሣት ይችላልና፤ ዮሐ.10፥14-18፤ ሉቃ. 23፥46። እነዚህ ጥቅሶች በወልድ ሁሉን ቻይነት ላይ ያተኩራሉ። በሰዎች ዘንድም ልጆች ሕይወታቸውን ከአባቶቻቸው የሚያገኙ መሆናቸው የወልድን ልጅነት ያንጸባርቃል፤ ሆኖም ለወልድ ልጅነት ከመጀመሪያ ነበረው፤ እርሱ ከዘለዓለም ነውና፤ ዮሐ. 1፥1። ክርስቶስ የአብ አንድያ ልጅ ነው። አንድያ የሚለው ቃል «ብቻውን የተወለደ» የሚለውን የግሪክ ቃል ሲተረጉም አንድ ብቻ በመሆኑ ላይ እንጂ በመወለዱ (ወይም በመገኘቱ) ላይ ማተኰር አይገባም፤ ዮሐ. 1፥14:18፤ 3፥16:18።

በአብና በወልድ መካከል ያለውን ፍቅር ለመረዳት አንድ መልካም ምድራዊ አባት ልጁን እንዴት እንደሚመለከተውና ምን እንደሚያደርግለት ማሰብ ሊረዳን ይችላል። አብ ወልድን ይወዳል፤ ዮሐ. 3፥35፤ 5፥20፤ 10፥17፤ 15፥9፤ 17፥22-24። እንደዚሁም ወልድ አብን ይወዳል፤ 14፥31። በምድራዊ አገላለጥ አብ ለወልድ ፍቅሩን የሚያሳየው :-

- በሕይወቱ ላይ ሙሉ ነጻነትን በመስጠቱ (ዮሐ. 5፥26፤ 10፥18)፥
- በራሱ ሥራ ውስጥ ለልጁ ትልቅ ኀላፊነት በመስጠቱ (5፥19-23)፥
- ልጁ የሚፈልጋቸውን ታላላቅ ነገሮች በመስጠቱ (6፥37:39፤ 17፥1-2)፥
- በልጁ ስም ለሚቀርቡለት ልመናዎች ሙሉ መልስ በመስጠቱ (16፥23)፥
- ልጁ ወደ ውጭ ሲሄድ፥ የክብር ስፍራው ለእርሱ በመጠበቁ (12፥28፤ 17፥5)፥
- ልጁ ወደ ታቀደለት አገልግሎት ሲሄድ ደስታውን በመግለጡ (12፥27-28፤ ደግሞም ማቴ. 3፥17፤ 17፥5)፥

- ልጁ በሚያደርገውና በሚያስተምረው ሁሉ የራሱን (የአባቱን) ፈቃድ ሲፈጽም በመደሰቱ (5፥19:30፤ 6፥38-39፤ 7፥16፤ 8፥27-28:40፤ 15፥10፤ 17፥4:6-8)፥

- የልጁን ወደ ቤት መመለስ በጕጉት በመጠበቁ (7፥33፤ 14፥28) ነው። ምድራዊ አባቶች የአብን አካላዊነት አርአያ ቢከተሉ ኖሮ፥ ልጆቻቸው እንዴት ይባረኩ ነበር!

2. የወልድ አካላዊነት

የወልድ አካላዊነት ልጅነት ነው። እርሱ የአብ አንድያ ውድ ልጅ ነውና። እርሱ አብን ይወዳል፤ ፍቅሩንም የሚያሳየው፥ የአብን ፈቃድ በሙሉ ልብ በመፈጸሙ ነው፤ ክርስቶስ፥ «አብን እንደምወድ፥ አባቴ ያዘዘኝንም እንደማደርግ ዓለም እንዲያውቅ ነው» በማለቱ በፍቅርና በመታዘዝ መካከል ያለውን ትክክለኛ የልጅነት መንፈስ አንጸባርቋል፤ ዮሐ. 14፥31 አ.መ.ት.፤ ዕብ. 5፥7-8። ክርስቶስ የአብን አሳብ በማስተማር፥ የአብን ሥራ በመሥራት፥ በተለይም ሕይወቱን ለሰው ኀጢአት መሥዋዕት በማድረግ፥ በሌላ አነጋገርም የአብን ፈቃድ በሙሉ ልብ በመፈጸም ትክክለኛውን የልጅነት መንፈስ ገልጧል። አብ በዚህ ሁሉ ተደስቷልና ከዚህ በላይ «1. የአብ አካላዊነት» በሚለው ርእስ አብ የተደሰተባቸው ነገሮች ተዘርዝረው ከጥቅሶቹ ጋር ይገኛሉ።

ክርስቶስ፥ «የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር» የሚለውን በማዛባት አንዳንዶች ወደ ልዩ ልዩ ስሕተት ገብተዋል፤ ዮሐ. 14፥28። እንግዲህ ከወልድ የአብ ብልጫ በምንድነው? በጥቅሱ ብልጫው የሚታየው ወልድ ወደ አብ በመሄዱ ነው። ይህም ብልጫው በሥራ ሂደት ውስጥ ነው፤ ወይም በምግባራዊ ሦስትነት አገልግሎት ነው። ክርስቶስ፥ «እኔና አብ አንድ ነን» (ዮሐ. 10፥30) ብሏልና ይህን አንድነት በህላዌ፥ በባሕርይ፥ በፈቃድ፥ በመለኮትና በአምላክነት አይተናል። በሌላ አነጋገር በአካልነት ተተካካዮች ናቸው። በዚህ ጥቅስ የተገለጠው ብልጫ ወልድ ሥጋ ከመልበሱ የተነሣ የሚታይ ብልጫ እንደሆነ ብዙዎች ያስባሉ። ሆኖም የአብ ብልጫ በአካላዊነት ነው ማለትም ይቻላል፤ ምክንያቱም ማናቸውም አባት ከልጁ በአመክንዮታዊ ቅደም ተከተል እንደሚበልጥ ሁሉ፥ አብም ከወልድ ይበልጣል። ይህም በባሕርይ፥ በህላዌ ... ወዘተ ሳይሆን በአካላዊነት ነው። ስለዚህ ሰው በሥላሴ ስም ሲጠመቅ አብ ይቀድማል፥ ወልድ ይከተላል፥ መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ ነው፤ ይህም ቅደም ተከተል ከዚህ በላይ እንዳየነው በሰው ደኅንነት ይገለጣል (ም. 25ለ 2ለ3 ይመ.)።

ዮሐንስ 14፥28 የመሳሰሉትን ጥቅሶች መፍታት በዚህ ዐይነት አተረጓጐም ሊረዳን ይችላል። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ»፥ «ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል» ብሎ ጽፏል፤ 1ቆሮ. 11፥3፤ 15፥28። «ትምህርተ ሥላሴ»ን በተመለከተ ስለ እነዚህ ጥቅሶች ሁለት ነገሮችን መናገር እንችላለን፤ መጀመሪያ የወልድን ምግባር ያመለክታሉ፤ ሁለተኛም እነዚህና የመሳሰሉት ጥቅሶች ህላዌያዊውን ሦስትነት በቀጥታ አያመለክቱም፤ ምክንያቱም እዚህ ላይ ወልድ በሥጋ ሆኖ ሥራውን ያከናውናል። ይህም የሥራው ሁኔታ በእንግሊዝኛ "MESSIANIC SONSHIP" («መሲሓዊ ልጅነት») ይባላል (3)።

### 3. የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት

መንፈስ ቅዱስ ከአብ ልዩ አካል መሆኑንና ሁሉን ቻይነት ያለው አካላዊ መንፈስ መሆኑን በዐጭሩ በዚህ ምዕራፍ ሀ3 አትተናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ «እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ፥ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ» በማለቱ አብ መንፈስ ቅዱስን አውጥቶ (አሥርጾ) እንደሚሰደው ገለጠ፤ ዮሐ. 15፥26። «ማውጣት» (ማሥረጽ)ን ለመረዳት «እፍ አለ» ከሚለው አሳብ ጋር ብናስተያየው ሊረዳን ይችል ይሆናል፤ ዘፍ. 2፥7፤ ዮሐ. 20፥22።

የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ከአብ ሁልጊዜ እየወጣ መሄዱ ነው። አብና መንፈስ ቅዱስ ሚናዎቻቸውን አይለዋወጡም። እዚህ ላይ የአብ አካላዊነት መንፈስ ቅዱስን ማውጣት ነው፤ የመንፈስ ቅዱስም አካላዊነት መውጣት (መሥረጽ) ነው። በወልድ መወለድና በመንፈስ ቅዱስ መውጣት መካከል ያለውን ልዩነት ማየት ይከብዳል። ሆኖም ምናልባት ልዩነቱ የልጁ መወለድ ከዘለዓለም ጀምሮ ቋሚ ሲሆን፥ የመንፈስ ቅዱስ መውጣት ግን ዘለዓለማዊ እንቅስቃሴ ነው ማለት ይቻላል።

በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት መካከል ያለውን ልዩነት ለመመርመርም ይከብዳል፤ ምክንያቱም የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ እንደሚወጣ (እንደሚሠርጽ) ሲያምኑ፥ ምሥራቃውያን ከአብ ብቻ እንደሚወጣ ያስተምራሉ። ምግባራዊ ሦስትነትን በተመለከተ ልዩነት የላቸውም፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ከአብ በወልድ አማካይነት ተልኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደሚመጣ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ይስማማሉ፤ ለዚህም በተለይ ዮሐ. 15፥26፤ ሐ.ሥ. 2፥33 ሊጠቀሱ ይችላሉ። ልዩነቱ ያለው ህላዌያዊው ሦስትነት ላይ ነውና ስለዚህ ልዩ ልዩ አሳብ እናቀርባለን። ይህ ልዩነት በእንግሊዝኛ የ "FILIOQUE" ሐረግ ይባላል፤ FILIOQUE በላቲን "And The Son" (እና ከወልድ) ማለት ነውና።

የመንፈስ ቅዱስ ምግባር የእግዚአብሔርን ዕቅድ ወደ ፍጻሜ ማድረስ ነው። ይህንም የሚያደርገው በክርስቶስ ምትክ አጽናኝ ሆኖ (ዮሐ. 14፥15-16:26) ሁሉን በማስተማር (14፥26)፥ የክርስቶስን ቃል በማሳሰብ (14፥26)፥ ስለ ክርስቶስ በመመስከር (15፥26)፥ የክርስቶስን አገልግሎት ስለማያስተውል ዓለምን በመውቀስ (16፥8-11)፥ ምእመናንን ወደ እውነት በመምራት፥ የሚመጣውን በመናገር (16፥13) እና ክርስቶስን በማክበር (16፥14) ነው። እዚህ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከክርስቶስና ከክርስቶስ ሥራ ጋር የተያያዘ መሆኑ ይታያል። እንግዲህ ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን «የክርስቶስ መንፈስ» እና «የጌታ መንፈስ» ብሎ በመጥራቱ ከክርስቶስ ቃል ጋር ይስማማል፤ ሮም 8፥9፤ 2ቆሮ. 3፥17።

መንፈስ ቅዱስ ምግባሩን ሲፈጽም፥ ክርስቶስ «የእውነት መንፈስ ... የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና»፥ «ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና» ብሎ ተናገረ። ይህንም ሲያብራራ፥ «ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ... ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ» በማለቱ ከአብ ጋር አንድነቱንና እርሱ ከአብ ተቀብሎ እንዳስተማረ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም የሚያስተምር መሆኑን አሳይቷል፤ ዮሐ. 16፥13-15ን ከ5፥19:30፤ 7፥16፤ 8፥28:40 ጋር ያስተያዩ።

መንፈስ ቅዱስ ከወልድ የወጣ (የሠረጸ) መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከሚቀርበው ጥያቄ አንጻር አራት ነጥቦችን ማተት ይገባል።

ሀ) ስለ ሦስቱ አካላት ከሚገልጹት ጥቅሶች መካከል አብዛኞቹ የሚናገሩት ስለ ምግባራዊ ሦስትነት ነውና ህላዌያዊውን ሦስትነት ቀጥታ የሚያሳዩት ጥቂቶች ናቸው።

ስለ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ህላዌያዊ ግንኙነት በግልፕ የሚናገር አንድም ጥቅስ አልተገኘም።

ለ) ብዙዎች ምግባራዊ ግንኙነት በህላዌያዊው ላይ ስለተመሠረተ፥ ስለ ህላዌያዊ ሦስትነት ቢያንስ ትልቅ ፍንጭ እንደሚሰጥ ያምናሉ። ለምሳሌ፥ «በአባቱ ዕቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» የሚለው አብንና በአብና በወልድ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለፕ ቃል ሥጋ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ነው ማለት ይችላሉ፤ ዮሐ. 1፥14:18። በተጨማሪም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በአብና በእርሱ፥ እንደዚሁም በወልድና በእርሱ መካከል ህላዌያዊውን ግንኙነት የሚገልፕ ይመስላቸዋል። እግዚአብሔር እንድናውቀው ይፈልጋልና ሥራው ሁሉ እርሱን ወደ ማወቅ ይመራል ማለት አመክንዮታዊ ሐቅ ነው። ሆኖም ይህ ሐቅ መጽሐፍ ቅዱስ ባይቃወመውም በቅዱሳት መጻሕፍት በግልፕ አልተረጋገጠም።

ሐ) መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ይወጣል የሚለውን ትምህርት በንድፍ እንደሚከተለው ማሳየት እንችላለን :-




ሆኖም ይህ አሳብ ሰው ያለ ወልድ እግዚአብሔርን ማወቅ ይችላል የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት እንዳያመጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚደርሰው በወልድ ነው፤ ዮሐ. 14፥6፤ ሐ.ሥ. 4፥12፤ 1ጢሞ. 2፥5።

መ) መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ይወጣል የሚለውን አሳብ በሁለት ንድፎች ልናሳየው እንችላለን :-







በስተቀኝ ያለው ንድፍ በክርስቶስ ጥምቀት የሆነውን ሊያሳስብ ይችላል፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ላይ ያረፈው ከአብ ወርዶ ነው። ሆኖም ከአብና ከወልድ መሥረጽ አንድ ዐይነት መውጣት አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከአብ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ቀጥተኛና ዘወትር የሚሆን መውጣት ነው። ከወልድ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ደግሞ ከአብ ከተገኘው ከወልድ እንጂ እንደ ወልድ በቀጥታ ከአብ አይደለም።

ምግባራዊ ሦስትነትን ስንመለከት፥ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ መንፈስ በመሆኑና መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አማካይነት ወደ ምእመናን ስለሚመጣ ምዕራባውያን «መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ወጣ» ለማለት በቂ ምክንያት መሆኑን ያምናሉ (4)።

ከአበው መካከል አብዛኞቹ የእግዚአብሔር ህላዌ የሚመሠረተው በአብ አካልነት ነው ብለው አመኑ። ይህን ያደረጉት ትምህርተ ሥላሴ በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ህላዌ መኖሩን እንዲያሳይና ሦስት አማልክት ወደሚል አመለካከት እንዳያመራ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ከወጣ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሁለት ህላዌዎች አሉ እንዳይባል ስለፈሩ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ወጣ አሉ፤ ሌሎችም መንፈስ ቅዱስ በወልድ አማካይነት ወጣ አሉ።

ይህም አስተሳሰብ ሌላ ጥያቄ ያስነሣል፤ ይኸውም በእግዚአብሔር ዘንድ መሠረታዊ ህላዌው የት ነው? የሚለው ነው። ከሦስቱ አካላት በአንዱ ከሆነ፥ ሌሎቹን ፍጹም አምላክ ማለት እንዴት እንችላለን? መበላለጥስ አያስከትልምን? የሚሉ ጥያቄዎችን ሊያነሡ ይችላሉ። እንደ እነዚህ ዐይነቶቹ ጥያቄዎች እንዴት ሊነሡ እንደቻሉና ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን ምን እንደወሰነች በምዕራፍ 27 እንመለከታለን። በመጀመሪያ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምረን መመልከት ይገባናል።

## መ) የሦስቱ አካላት ግንኙነት (5)

ሦስቱ አካላት በአንድነት እንደሚሠሩ አይተናል። አንድ ምግባር በተለይ የአንደኛው አካል ቢሆንምና ያው አካል ብቻውን የሠራው ቢመስልም፥ ሌሎች ሁለቱ አካላት አጠገቡ እንዳሉ አስተውለናል (ም. 26 ለ1)። ይህም ምግባራዊ ሦስትነትን ሲያመለክት፥ አንዳንድ ጥቅሶች ግን በተለይ ህላዌያዊውን ሦስትነት ያሳያሉ።

. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ፊልጶስ መልስ ሲሰጥ፥ «እኔን ያየ አብን አይቷል» የሚለውን ምሥጢር ከተናገረ በኋላ በመጀመሪያ ለፊልጶስ፥ በኋላም ለሐዋርያት በአንድነት ሁለት ጊዜ፥ «እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ» በማለት ምሥጢሩን በመጠኑ ገለጠው፤ ዮሐ. 14፥10-11፤ 17፥20-21። ክርስቶስ በትምህርቱ፥ «የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው»፤ «እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል»፤ «እኔና አብ አንድ ነን» በሚሉት ሐረጎች አብና ወልድ ሳይደባለቁ እርስ በርሳቸው እንደሚኖሩ ለሐዋርያት አሳየ፤ ዮሐ. 8፥16፤ 12፥45፤ 10፥30። ይህም ብቻ ሳይሆን፥ «የእውነት መንፈስ ... ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር» እና «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም እንመጣለን» ስለሚል፥ በሦስቱ አካላት መካከል አካልነታቸው ሳይደባለቅ ውሳጣዊ የእርስ በርስ ህላዌ እንዳለ ማስተዋል አይከብድም፤ ዮሐ. 14፥17:23። ስለዚህ ኢየሱስ፥ «እኔን ያየ አብን አይቷል»፥ «እኔንስ ብታውቁኝ አባቴም ደግሞ ባወቃችሁ ነበር» በማለቱ ከሦስቱ አንዱን ብቻ ማወቅ አለመቻሉን ገልጧል፤ 14፥9፤ 8፥19። ይህ የሦስቱ አካላት ውሳጣዊ የእርስ በርስ አካልነት በግሪክ ቋንቋ "PERICHORESIS"፥ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ደግሞ "CO-INHERENCE" ይባላል። በሦስቱ አካላት ያለውን ይህን ውሳጣዊ የእርስ በርስ አካልነት ብናስተውል፥ ልዩ ልዩ አሳብ ያስከትላል።

ለእግዚአብሔር ህላዌ ከሦስቱ አንዱን (አብን ወይም ወልድን ወይም መንፈስ ቅዱስን) መሠረት ማድረግ አያስፈልግም። በሌላ አነጋገር ህላዌያዊውን ሦስትነት በተመለከተ ከሦስቱ አንዱን ራስ፥ ምንጭ፥ መነሻ ... ምክንያት ማድረግ አይገባም። ለእግዚአብሔር ምክንያት የለም፤ እርሱ አለና። እግዚአብሔር ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአንድነት ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖሩ

ናቸው የሚል መልስ አለ። ሦስቱ አካላት በአንድነት የእግዚአብሔር ህልውና ናቸው። እግዚአብሔር አንድ ነው፤ እግዚአብሔር ሦስት ነው ማለት ይቻላል።

የሦስቱን ግንኙነት በሦስት አሳብ ለማጠቃለል እንሞክር :-

1ኛ. ከፍ ያለ ኅብረት አላቸው፤ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ብዙ ነገር በአንድነት ይይዛሉ፤ አምላካዊ ህልውናቸውን፥ አምላካዊ ባሕርያቸውንና አምላካዊ አገዛዝን በአንድነት ይይዛሉ። ለምሳሌ እግዚአብሔር ወልድ በዙፋኑ መካከል አለ፤ ለእርሱ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶታል፤ ራእ. 7፥17፤ ማቴ. 28፥18። ዮሐንስ በራእዩ «ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ መስተዋት የጠራውን የሕይወት ውሃ ወንዝ» በማየቱ የሦስቱን ሥልጣን በአንድነት ይገልጣል፤ ራእ. 22፥1 አ.መ.ት.። ክብርንም ፍቅርንም በአንድነት ይይዛሉ፤ እያንዳንዱ ሌሎቹን ይወዳል፤ እያንዳንዱ ሌሎቹን ደስ ያሰኛል።

2ኛ. እያንዳንዱ በሌሎቹ ውስጥ ይኖራል፤ ይህም ብቻ ሳይሆን አካላዊነቱ ሳይከፋፈል በስሜት፥ በአሳብ፥ በፈቃድ እያንዳንዱ በሌሎች ውስጥ ይኖራል ማለት ነው። ሰዎች ሲፋቀሩ መፋቀራቸውን ምናልባት በአነስተኛ መጠን ለማወቅ ይጀምራሉ። ባልና ሚስት «አንድ ሥጋ ይሆናሉ»፤ ነገር ግን ክርስቶስ «እኔ በአብና አብ በእኔ» ወደሚለው የላቀ የግንኙነት ደረጃ ለመድረስ ከሩቅ ሆነው ምናልባት ማሰላሰል ይችላሉ።

3ኛ. በሦስቱ መካከል የሚዘዋወር አምላካዊ ሕይወትና ኀይል አለ፤ እርሱ ሕያው አምላክ ነውና፤ ዘዳ. 5፥26፤ ኢያሱ 3፥10፤ 1ሳሙ. 17፥26፤ ማቴ. 16፥16፤ 26፥63፤ ዮሐ. 6፥35፤ 2ቆሮ. 3፥3፤ ዕብ. 10፥31፤ 12፥22፤ ራእ. 7፥2። ይህም ከ«ራስ» ወይም ከዋናው አካል ዝቅ ወዳሉት የሚፈስ አይደለም። ይህን አሳብ በንድፍ ለመግለጥ ብንፈልግ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል :-




ሆኖም ማናቸውም ንድፍ ወይም ምሳሌ ቅድስት ሥላሴን አሟልቶ መግለጥ አለመቻሉን መገንዘብ ይገባናል። የሦስቱ አካላት ውሳጣዊ የእርስ በርስ ግንኙነት ትምህርት ለመተርጐም የሚያስቸግሩ አንዳንድ ጥቅሶችን ያብራራል። ለምሳሌ ክርስቶስ፥ ሰዎች በአጋንንት አለቃ አጋንንትን እንደሚያወጣ በመናገራቸው፥ «በሰው ልጅም ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን አይሰረይለትም» ብሎ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጣቸው፤ ሉቃ. 12፥10፤ ማር. 3፥22-29። እዚህ ላይ «የሰው ልጅ» አካላዊ እንደሆነ ሁሉ፥ መንፈስ ቅዱስም አካላዊ መሆኑ ይታያል። ሰዎች ክርስቶስን ሲመለከቱት ሰው ነበረና ስለ እርሱ ሲጠራጠሩና

ሊሳሳቱ ይችላሉ፤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ግን ግልጥ የሆነ አምላካዊ ሥራ በመሆኑ፥ «የሰይጣን ሥራ ነው» በማለታቸው ዐውቀው የእግዚአብሔርን ሥራ መካዳቸውን ልናስተውል ይገባናል። ከዚህም ጋር አብና ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመኖራቸው፥ ሦስቱን በአንድነት ከደው ነበርና ይህን በማድረጋቸው ለንስሓ ዕድል አይሰጣቸውም፤ ዐውቆ የእግዚአብሔርን ሥራና ፈቃድ መካድ አስፈሪ የሆነ ውጤት ያስከትላልና፤ ዕብ. 12፥17።

ስለ ቅድስት ሥላሴ ብዙ ነገር ቢገለጥም፥ ከምድራዊ አሳብ በላይ ነውና ምሥጢር ነው። ዓላማችን በስሕተት እንዳይሰጥሙ ለምእመናን የውቅያኖስ ዳርቻ የት እንደሆነ ማሳየት፥ ከዚህም በላይ እንደ ዐቅማቸው ዋኝተው ለተገለጠው ትክክለኛ የአምልኮት መልስ እንዲሰጡ ማድረግ ነው። በሚከተለው ምዕራፍ ቤተ ክርስቲያን ይህን የሥራ ኀላፊነት በአግባቡ ትወጣ ዘንድ ምን እንዳደረገች እናያለን።

## ማስታወሻ

(1) «እግዚአብሔር ወልድ» በሚለው መጽሐፍ በም.3 ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑን በዝርዝር ማሳየት ሞክረናል።

(2) C.T. ገጽ 143-145።

(3) የዚህን አተረጓጐም አጠቃቀም በዚህ ምዕራፍ ሀ2 ውስጥ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ...» በሚለው ሐረግ አሳይተናል። ደግሞም ስለ 1ቆሮ. 12፥28 ትርጕም «እግዚአብሔር ወልድ» ሁለተኛ እትም ገጽ 66-67 በሚለው መጽሐፍ ገልጠናል።

(4) ዓሥራት ገብረ ማርያም በ«ትምህርተ መለኮት» ገጽ 59-63 ላይ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ስለ መውጣቱ ክርክር አቅርበዋል። ዮሐ. 15፥26፤ 14፥17:26፤ 16፥15፤ 20፥22፤ 16፥14፤ ገላ. 4፥6። መንፈስ ቅዱስ በወልድ እንደተላከ እንጂ ከወልድ እንደወጣ አያሳዩም ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ይወጣል ወይም ከወልድ ይወጣል ወይም አይወጣም አይልም። ከወልድ ይወጣል የሚሉት በጊዜ ውስጥ፥ በተለይ ሰውን በማዳን ሥራ ላይ የክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ ምግባራዊ ግንኙነት በዘለዓለማዊ ሁኔታ ካለው ከወልድ የመንፈስ ቅዱስ መሥረጽ ጋር የሚስማማ መሆኑን ይቀበላሉ። ብዙዎች ይህን ክርክር ሲመለከቱ፥ ክርክሩ በመሠረቱ ከፍጥረት በፊት የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ግንኙነት የሚመለከት በመሆኑ ለአብያተ ክርስቲያናት መለያየት በቂ ምክንያት አለመሆኑን ይናገራሉ፤ ለምሳሌ GRUDEM ገጽ 247 ይመ.

(5) በዚህ ክፍል hBYG ገጽ 203-204 ብዙ አሳብ ተገኝቷል።

# ምዕራፍ 27 - ትምህርተ ሥላሴ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ሥላሴ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ባይገኝም፥ ትምህርተ ሥላሴ የነገረ መለኮት ዐቢይ ርእስ መሆኑን አይተናል። እንደዚሁም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ምን ያህል ትምህርተ ሥላሴን እንደተረዱት ባናውቅም፥ በአንድ እግዚአብሔር ሦስት አካላት እንዳሉ አምነው የመለኮትን አንድነትና የአካል ሦስትነትን ለትምህርታቸው መሠረት አደረጉቸው።

ወንጌል ሲስፋፋና በግሪክ ቋንቋ ሲሰበክ፥ መምህራን ምሥጢሩን ለማብራራትና ለመወሰን ሲፈልጉ በቂ የሆኑ ቃላት አልነበሯቸውም። በዚህ ምክንያት አዲስ ቃላትን አዘጋጁ፤ ለምሳሌ ሦስት አካላት በአንድ አምላክ መኖራቸውን ለመግለጥ ሲፈልጉ፥ ሥላሴን የሚተረጉመው ቃል ተፈጠረ። ደግሞም ከተለመደው የግሪክ ቋንቋ በተገኙት ቃላት እየተጠቀሙ ለእነዚህ ቃላት ከቀድሞው የሚበልጥ ትርጉም ሰጧቸው። ይህም በቋንቋዎች ዕድገት የሚታይ ሂደት ነው። ለምሳሌ ይህን ብዙ በምንጠቀምበት አካል በተተረጎመበት PERSONA በሚለው የላቲን ቃል ማየት እንችላለን። PERSONA፥ ተዋናይ ባሕርዩን የሚወክለውንና የሚገልጠውን በፊቱ ላይ የሚያደርገውን ሽፋን በመጀመሪያ አመለከተ። ከዚያም በኋላ ቃሉ ተዋናዩን ራሱን ማመልከት ጀመረ። ቀጥሎም በሕግ የሚጠየቅና ግብረገባዊ ኀላፊነት ያለበት ፍጡር ማለት ሆነ። በዚህ አጠቃቀም PERSONA ከእንስሳትና ሕይወት ከሌለበት ከማናቸውም ነገር ተለየ (1)። አሁን በ«አካል» የተተረጐመው የእንግሊዝኛ ቃል PERSON በዚህ መጽሐፍ ያለውን ሰፊ አሳብ ሊይዝ ችሏል (ም.25 መ1 ይመ.)። በርግጥ አካል በአማርኛ ብዙ ትርጉም አለው፤ ነገረ መለኮትን በተመለከተ ግን ለአካል ሰፊና ጠለቅ ያለ ትርጉም ልንሰጠው እንሞክራለን። እንግዲህ የአንድ ቃል አጠቃቀም እየተለወጠና አሳቡ እየተስፋፋ ስለሚሄድ፥ የዱሮ ዘመን ሰዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ማስተዋል እንጂ የራሳችንን አጠቃቀም ለእነርሱ ቃላት ማዋል አይገባም። ማናቸውም ጸሐፊ፥ አንባቢዎቹ በቃላቱ በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ማስተዋል እንዳለባቸው ተስፋ ያደርጋልና፤ አለበለዚያ አሳቡን በትክክል ማግኘት አይችሉም።

ወንጌል በመጀመሪያ ሲሰበክ ብዙ ሰዎች ያቀርቡት የነበረው ጥያቄ፥ «ስለ የትኛው አምላክ ይናገራል?» የሚል ነበር፤ ሐ.ሥ. 17፥18። አንድ የአይሁድ ሰው ክርስቲያንን «የአንተ አምላክ ከአብርሃም፥ ከይስሐቅና ከያዕቆብ አምላክ ጋር እንዴት ይገናኛል?» ወይም «አይሁድና ክርስቲያኖች አንድን አምላክ ያመልካሉ?» ብሎ ሊጠይቅ ይችል ነበር። ወንጌል ወደ አሕዛብ ሲደርስም ወንጌልን ከአሕዛብ ሃይማኖቶች መለየት አስፈላጊ ነበረ። በሁለተኛው መቶ ዓመታት የግኖስቲክ አስተሳሰብ የወንጌል መልእክተኞችን የሚቀናቀን ሃይማኖት ነበረ። የግኖስቲክ ተከታዮች ልዩ ልዩ አሳብ ቢኖራቸውም፥ እንደ ክርስቲያኖች እያንዳንዱ ሰው የራሱን መዳን መከታተል ባለበት አሳብ ላይ ያተኩሩ ነበር። ሆኖም ስለ እግዚአብሔር ያላቸው አሳብ የተለያየ ነበረ። ግኖስቲኮች በሁለት አማልክት አመኑ፤ አንዱ አምላክ ዓለምን የፈጠረ፥ ሁለተኛው ደግሞ ዓለምን የሚያድን ነበር። ይህን ሲያምኑ የሚበዙቱ ለሁለተኛው አምላክ ትኵረት በመስጠት ታችኛውን ወይም ዝቅተኛውን ፈጣሪ አምላክ አደረጉት።

ይህ ለክርስቲያን መምህራን አደገኛ ትምህርት ነበረ፤ ምክንያቱም የብሉይ ኪዳን አምላክ ለዓለም ፍጥረት ብቻ ኀላፊ ሲሆን፥ የአዲስ ኪዳን አምላክ ለደኅንነት ኀላፊ በመሆኑ ብልጫ እንዳለው እንዳይታሰብ መጠንቀቅ ነበረባቸው። ግኖስቲካዊ አስተሳሰብ

የክርስቲያንን እምነት እንዳይበክል፥ ኢሬኔየስ (IRENAEUS) የብሉይና የአዲስ ኪዳን አምላክ አንድ አምላክ መሆኑን በአጽንዖት አስገነዘበ። አንድ አምላክ ዓለሙን ፈጠረ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን ዋጀው፤ በመንፈሱም በተከታዮቹ ይኖራል ብሎ አስተማረ። እንግዲህ ትምህርተ ሥላሴ አማኞች ያወቁትን፥ ያመለኩትንና የወደሱትን አምላክ ስለሚያሳይ፥ ቤተ ክርስቲያንን ከተቀናቃኞቿ ለያት (2)። እስከ ዛሬ ድረስም ትምህርተ ሥላሴ እውነተኛ የክርስቲያንን ሃይማኖት ከሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ይለያል።

አበው የክርስቲያንን ትምህርት ለመወሰን ሲሞክሩ ዋናው ትግላቸው በአንድ አምላክ ሦስት አካላት መኖራቸውን ማሳየት ነበረ። በዚህ ውስጥ ሁለት ምሥጢራት ነበሩ፤ እነርሱም ምሥጢረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ ናቸው። እነዚህ ምሥጢራት የተያያዙ ቢሆኑም፥ በዚህ ምዕራፍ ትምህርተ ሥላሴን የሚመለከተውን ብቻ በዝርዝር ለማተት እንፈልጋለን፤ ትምህርተ ሥጋዌን ግን በሚከተለው መጽሐፍ እንመለከተዋለን።

## ሀ) የትምህርተ ሥላሴ ግንዛቤ ሂደት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ከአሕዛብ ሃይማኖትና ፍልስፍና ጋር ስታገናኝና ቅዱሳት መጻሕፍትን ስታጠና በልዩ ልዩ አገር ስለ ቅድስት ሥላሴ የተለያየ ትምህርት ተነሣ። ትምህርቱ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ስምምነት እስኪገኝ ድረስ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እየተወገዙ ረጅምና ከባድ ትግል ይካሄድ ነበር። በዚህ ታሪክ ውስጥ ዋና ዋና ሰዎችን፥ የተለዩ ስሕተቶችን፥ ጉባኤዎችንና የተላለፉ ውሳኔዎችን በቅደም ተከተል ለመዘርዘር እንሞክራለን።

### 1. ኢሬኔየስና ግኖስቲካውያን

ኢሬኔየስ በፈረንሳይ አገር ጳጳስ የነበረ ሲሆን ዋና አገልግሎቱ ከ175-195 ዓ.ም. ነው። ከዚህ በላይ እንዳየነው የብሉይ ኪዳን አምላክና የአዲስ ኪዳን አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ መሆኑን በጽሑፎቹ በማስተማር ግኖስቲካዊ ትምህርትን አጥብቆ ተቃውሟል (2)።

### 2. ተርቱሊያንና የሰባልዮስ ስሕተት

ተርቱሊያን (TERTULLIAN) በካርቴጅ በሰሜን አፍሪካ ከ165-218 ዓ.ም. ገደማ በማገልገል በላቲንና በግሪክ ቋንቋዎች ብዙ የክርክር መጻሕፍትን ጻፈ። በላቲን ቋንቋ የጻፋቸው ሠላሳ አንድ መጻሕፍት በዚህ ቋንቋ የመጀመሪያው የላቲን ክርስቲያናዊ ስብስብ ነበረ። ስለ ልዩ ልዩ ነገር ትምህርቱን መቀበል ባንችልም፥ ለሥላሴና ለትሥጉት ልዩ ልዩ ቃላት በማዘጋጀት የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲያድግ አደረገ። በፕራክሲየስ (PRAXEAS) ላይ የጻፈው (210 ዓ.ም. ገደማ) የክርክር መጽሐፍ አስቀድሞ ከተጻፉት መጻሕፍት ይልቅ የቅድስት ሥላሴን ትምህርት በሚገባ አብራርቷል (3)።

ፕራክሲየስና ሰባልዮስ በሮም የእግዚአብሔርን አንድነት ለመጠበቅ እግዚአብሔር እንደ አብ፥ እንደ ወልድና እንደ መንፈስ ቅዱስ በሦስት ሚናዎች ራሱን ሲገልጥ፥ አንድ አካል ብቻ መሆኑን አስተማሩ። ይህ ትምህርት በእስያ የተጀመረ ይመስላል፤ በ2ኛውና በ3ኛው መቶ ዓመታት ብዙ ተከታዮች ነበሩት። ስለ ፕራክሲየስ ትምህርት ተርቱሊያን፥ «አጽናኙን አባረረ፤ አብን ሰቀለ» ብሎ በዘበት ይህ ትምህርት ከሥላሴ እውነተኛ ትምህርት ጋር ፈጽሞ እንደማይስማማ አጋለጠ (4)።

ትምህርቱ ዛሬ የሚታወቀው በሰባልዮስ ስም ነው። ትምህርቱ በልዩ ልዩ ዐይነትና ስም ቢታወቅም፥ ዋና አሳቡ እግዚአብሔር በሦስት መልክ ወይም ሚና ራሱን ገልጧል እንጂ አካላዊ ሦስትነት የለውም የሚል ነው። አሁን በኢትዮጵያ በኢየሱስ ስም ብቻ የሚያጠምቁ ማኅበረ ሐዋርያት በሚል ድርጅት ስም የሚጠሩት ይህን ትምህርት ያስተምራሉ።

ይህን ትምህርት ለመቃወም በምዕራፍ 26ሐ ስለ አብ፥ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት የተጠቀሱትን ጥቅሶች ማብራራት ዋና መንገድ ይሆናል።

3. ቅዱስ አትናቴዎስና የአርዮስ ስሕተት

ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሥላሴን በመወሰን ረገድ ያጋጠማት ዋናው ክርክር የአርዮስ ነበረ። አርዮስ በ336 ዓ.ም. ሞተ፤ ሆኖም ከሞተ በኋላ ትምህርቱ ቢያንስ እስከ 381 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያን ብዙ ተከታዮች ነበሩት። ቅዱስ አትናቴዎስ ከ296-373 ዓ.ም. ኖረ።

የአርዮስ ትምህርት ከትሥጉት በፊት ስለነበረው ስለ «ቃል» ነበረ። ይህን አሳብ በተለይ በትምህርተ ሥጋዌ እናትታለን። ሆኖም ትምህርተ ሥላሴን በሚመለከት አርዮስ፥ ሁለተኛው አካል አንድያ ልጅ ቢሆንም፥ ዓለም ሳይፈጠርም ቢኖር፥ ያልተገኘበት ጊዜ ነበረ፤ ስለዚህ ፍጡር በመሆኑ ከዘለዓለም ፍጹም አምላክ አልነበረም በማለት የስሕተት ትምህርት አስተማረ። ቅዱስ አትናቴዎስ ግን ይህን ትምህርት እየተቃወመ ከብዙ ትግል በኋላ አርዮስን አሸነፈው። አትናቴዎስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ባይሆን ኖሮ እርሱን ማምለክ አይገባም ነበር፤ ፍጹም አምላክም ባይሆን ኖሮ አዳኝ መሆን አይችልም ነበር በማለት ስለ ክርስቶስ አምላክነት የነበረውን ግንዛቤ ገልጧል። አትናቴዎስ ብዙ መጻሕፍትን ጽፏል። እርሱ የእስክንድርያ ጳጳስ የእስክንድር ጸሓፊ በመሆኑ በኒቅያ ጉባኤ ተሳትፎ ድምፅ ባይሰጥም፥ በማስታወሻዎቹና በጳጳሱ ትእዛዛት የጻፋቸው መመሪያዎች በጉባኤው ውጤት ትልቅ ድርሻ ነበራቸው።

የጉባኤው ዋና ውጤት በኒቅያ ጸሎተ ሃይማኖት ይታያል (ለ. ይመ)። ከኒቅያ ጉባኤ (325 ዓ.ም.) በኋላ ሌላ ከባድ ክርክር ተነሣ፤ ቅዱስ አትናቴዎስ ግን ለትክክለኛው ትምህርተ ሥላሴ ዋና ጠባቂ ሆነ፤ የትግሉ ፍሬ የታየውም ከሞተ በኋላ ስምንት ዓመታት ቈይቶ በ381 ዓ.ም. በቊስጥንጥንያ ጉባኤ ነበረ፤ በዚያ ጉባኤ ውሳኔ ትምህርተ ሥላሴ ከኒቅያ ጉባኤ ይልቅ የጸና መሠረት አገኘ፤ በተለይም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር የሚስተካከል በመሆኑ ፍጹም አምላክነቱ ታወጀ (5)።

የአርዮስ ትምህርት በየጊዜው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነሣል። ዛሬ በተለይ «የይሖዋ ምስክሮች» እንደ አርዮስ ክርስቶስ ፍጡር እንጂ ፍጹም አምላክ አይደለምና መንፈስ ቅዱስ አካላዊ አይደለም በማለታቸው ትምህርተ ሥላሴን አይቀበሉም (6)። አርዮስ እንዳደረገው አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ቢጠቅሱም አተረጓጐማቸው ውድቅ ነው፤ ምክንያቱም ትምህርታቸው ከብዙ ሌሎች ጥቅሶች ጋር አይስማማም። የታወቀውን ከጥንት የተጀመረውን ትምህርተ ሥላሴ በምዕራፍ 25 እና 26 ለማተት ሞክረናል፤ በተለይም 26 ሐ ይህን ስሕተት በግልጥ ማሳየት ይችላል።

4. ቅዱስ አውግስጢኖስ (354-430 ዓ.ም.)

ቅዱስ አውግስጢኖስ ከላቲን አበው ታላቁ እንደሆነ ይታሰባል፤ ምክንያቱም ትምህርቱና የጻፋቸው መጻሕፍቱ በምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ለብዙ መቶ ዓመታት ቋሚና መደበኛ ምስክር ሆነዋል። በ396 ዓ.ም. በሰሜን አፍሪካ በሚገኘው ሂፖ ጳጳስ ሆኖ በአገረ ስብከቱ በመኖር አገልግሎቱን ፈጸመ።

አውግስጢኖስ ስለ ትምህርተ ሥላሴ በሰፊው ሲጽፍ፥ በተለይ እንደ ሰባልዮሳዊ ወይም እንደ አርዮሳዊ ትምህርት መቃወም ሳይሆን ለምእመናን ምሥጢሩን መፍታት ሞክሯል። ይህንም ሲያደርግ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» የሚለውን ጥቅስ ሲመረምር፥ አብ ወዳጅ፥ ወልድ ተወዳጅ ሲሆኑ፥ መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ መካከል ያለው ግንኙነት ነው የሚለውን ማብራሪያ አቀረበ። በዚህ ምሳሌ አብና ወልድ አካላት ሲሆኑ «ግንኙነት»ን አካል ማለት ይከብዳል፤ ስለ አንድ ግንኙነት ስንናገር «እርሱ»፥ ወይም ለግንኙነት «አንተ» (ወይም «አንቺ») ብሎ መናገር ትርጉም አይሰጥም። ከዚህ የተነሣ ብዙ ሊቃውንት አውግስጢኖስ (እና ሌሎች አባቶች) በመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት የሚያምን አይመስላቸውም።

ነገር ግን ምንም እንኳ የአውግስጢኖስ አሳብ ረቂቅ ቢሆንም፥ በብዙ ሌሎች አንቀጾች በመንፈስ ቅዱስ አካልነት የሚያምን መሆኑ ታይቷል። ለምሳሌ፥ «... እርሱ (መንፈስ ቅዱስ) ለአንድ ሰው ከመሰጠቱ በፊት ከአብና ከወልድ ጋር ከዘለዓለም እግዚአብሔር ነበረ። እነርሱ በመስጠታቸውና እርሱ በመሰጠቱ ከእነርሱ አያንስም። እርሱ የእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ ቢታይም፥ እርሱ ራሱ ሰጪ እግዚአብሔር ነው» ብሎ ጻፈ (7)።

ከአበው መካከል እንደ ብዙዎቹ አውግስጢኖስ የእግዚአብሔርን አንድ አምላክነት ለመጠበቅ አብ የሥላሴ ምንጭ ወይም መነሻ መሆኑን አመነ። ይህም አንድነት ምሥጢራዊነት ያለው መሆኑን ያስተዋለ አይመስልም። ሆኖም በቅድስት ሥላሴ በግልጥ አመነና ትምህርቱ ለምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት ታላቅ በረከት ሆነ (8)። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርጸት አውግስጢኖስ የሰጠውን ትምህርት ከዚህ በታች እናትታለን።

5. የደማስቆው ዮሐንስ (675-749 ዓ.ም.)

ዮሐንስ ከምሥራቃውያን ታላላቅ አበው የመጨረሻው ነበረ። ከእርሱ በፊት የነበሩትን ትምህርት መርምሮ ውጤታማ አደረገው።

አርጌንስ (185-254) የእግዚአብሔርን አንድ አምላክነት ለመጠበቅ አብ በራሱ እግዚአብሔር ሲሆን ወልድ በምሳሌው ተወለደ፤ ይህም ማለት አብ መጀመሪያ መነሻ ሳይኖረው፥ ወልድ መጀመሪያ ወይም አንድ ዐይነት መነሻ ነበረው የሚለውን አስተማረ። ከዚያም ቀጥሎ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ እንደወጣ አስተማረ። አርጌንስ ይህን ሲያስተምር፥ አብ በራሱ ያለ መነሻ እግዚአብሔር ሲሆን (AUTOTHEOS)፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግን መነሻ ነበራቸው፤ ሆኖም ከዚህ አሳብ በስተቀር ወልድና መንፈስ ቅዱስ እንደ አብ በመሆናቸው ፍጹም አምላክነታቸውን ለመጠበቅ ሞከረ። የአርጌንስን ትምህርት በሚከተለው ንድፍ ልናሳይ እንችላለን ፦



አርዮስ የአርጌንስን ትምህርት ወደ አንድ አቅጣጫ ጐትቶ ክርስቶስ ፍጡር መሆኑንና መንፈስ ቅዱስ አካላዊ አለመሆኑን እንዳስተማረና ቅዱስ አትናቴዎስ ግን በእስክንድርያ ሳለ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይህን ትምህርት እየተቃወመ እንዳሸነፈ አይተናል፤ ም.27 ሀ3።

በቀጰዶቅያ (ከጠርሴስ በስተ ሰሜን የነበረው አውራጃ) ይኖሩ የነበሩ ሦስት አባቶች፥ ታላቁ ባስል (329-379)፥ ወንድሙ የኒያሳው ጎርጎርዮስ (330-395) እና የአንዚናዙ ጎርጎርዮስ (330-389) አርዮሳውያንን ሲቃወሙ፥ ትምህርተ ሥላሴን አብራሩት። እነዚህ ቀጰዶቃውያን አርጌንስ በተናገረው ዐይነት የሥርጸትን ሂደት ማብራራት አይቻልም በማለት ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣታቸውን አስተማሩ። ትምህርታቸውን በሚከተለው ንድፍ ለማሳየት እንሞክራለን :-




የዚህ አገላለጥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ግንኙነት ባለማሳየቱ፥ የኒያሳው ጎርጎርዮስ አስተሳሰብ መንፈስ ቅዱስ የሠረጸው ከአብ በወልድ በኩል እንደሆነ የሚያመለክት ነው። የደማስቆው ዮሐንስ ይህን አስተሳሰብ በትምህርቱ አካትቶታል። ይህንም አሳብ በንድፍ እንደሚከተለው ልናሳየው እንችላለን :-




የቀጰዶቅያውያንንና የአውግስጢኖስን አስተሳሰብ እንደሚከተለው መግለጥ ይቻላል :-

| ቀጰዶቅያውያን | አውግስጢኖስ |
|---|---|
| - አብ ያልተወለደ ነው | - አብ ወልድን በመውለዱ አብ ነው |
| - ወልድ ከአብ የተወለደ ነው | - ወልድ ከአብ በመወለዱ ልጅ ነው |
| - መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሠርጻል | - መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ መካከል ያለ ትስስር በመሆኑ ከአብና ከወልድ ይሠርጻል |

የቀጰዶቅያውያንንና የአውግስጢኖስን አስተሳሰብ በንድፍ ብናሳየው ደግሞ እንደሚከተለው መሆን ይችላል :-









በአጠቃላይ አውግስጢኖስ ስለ ቅድስት ሥላሴ ያለው አሳብ ግልፕ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ አሳቡ በ(ሐ) ላይ የተገለጠውን ይመስላል። ተከታዮቹ ግን አባታቸው የመንፈስ ቅዱስን ፍጹም አካላዊነት እንዳስተማረ ለማሳየት ትምህርቱ በ(መ) ላይ ከሚታየው ጋር የተቀራረበ መሆኑን ገለጡ (9)።

የደማስቆው ዮሐንስ ውሳጣዊ የእርስ በርስ ህላዌን አስተምሮ PERICHORESIS (በእንግሊዝኛ CO-INHERENCE) በሚለው የግሪክ ቃል አብራራው። ይህን ትምህርት ቢከታተል ኖሮ የእግዚአብሔር ህላዌ በሦስቱ አካላት በአንድነት ያለ እንጂ በአብ (ወይም በወልድ ወይም በመንፈስ ቅዱስ) የሥላሴ ህላዌ አለመሆኑን ያስተምር ነበር ብለን ማሰብ እንችላለን። በዚህም መሠረት በምዕራባውያንና በምሥራቃውያን መካከል ስለ መሥረጽ ለተፈጠረው መለያየት ምናልባት መፍትሔ ይገኝ ነበር።

የኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት መንፈስ ቅዱስ ከአብ መሥረጹን ዐወጀ። ሆኖም በምዕራባውያንና በምሥራቃውያን መካከል የመንፈስ ቅዱስን ሥርጸት አስመልክቶ ልዩነት እንዳለ ግልፕ ነው። የቍስጥንጥንያው ፓትሪአርክ ፎርቲየስ (864-867 እና 880-886) መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠረጸ ብሏል፤ ሆኖም «ብቻ» የሚለው ቃል በምሥራቃውያን ዘንድ ለኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት አልተጨመረም። ምዕራባውያን ግን ሥርዐተ ሃይማኖቱን ሲደግሙ «እና ከወልድ» (FILIOQUE) የሚለውን ሐረግ ቀስ በቀስ መጨመር ጀመሩ። በሦስተኛው ቶሌዶ (በእስፓኝ) በ589 ዓ.ም. «እና ከወልድ» ለኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት ተጨመረ። የሮም ጳጳስ ቤነዲክት በ1017 ዓ.ም. የሐረጉን መጨመር ፈቀደና በትምህርት በኩል በምዕራብና በምሥራቅ መካከል ለነበረው መለያየት ዋና ምክንያት ሆነ። ከ1054 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መለያየቱ ጸንቷል። አስቀድሞ እንደተገለጠው ብዙ ምእመናን ስለ ሥርጸቱ ያለው የተለያየ አሳብ እጅግ ረቂቅ በመሆኑ ለመለያየቱ በቂ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ይስባሉ። ሆኖም ከነገረ መለኮት መለያየት በስተጀርባ የፖለቲካ ትግል ነበረ፤ ይህም የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ከሮም ጳጳስ ጋር የሥልጣን እኩልነት እንዳለው መታሰቡ ነው (10)።

ከደማስቆው ዮሐንስ በኋላ በምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ስለ ቅድስት ሥላሴ ብዙ አዲስ አሳብ አልተነገም።

6. አንሰልም (1033-1109) እና አኩናስ (1224-1274)

አንሰልም ቅድስት ሥላሴን በፍልስፍና መንገድ እንደሚከተለው ለማብራራት ሞከረ። ወልድ ከአብ ስለሚወጣ አብ አይደለም። መንፈስ ቅዱስም ከአብ ስለሚወጣ አብ አይደለም። ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ስለሚወጡ ምን ልዩነት አላቸው? ልዩነት አለ ማለት የሚቻለው አንዱ ከሌላ ቢወጣ ብቻ ነው። እንግዲህ ወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ስለማይወጣ መንፈስ ቅዱስ ከወልድ ይወጣል። በአብና በወልድ መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ የተቀራረበ በመሆኑ ከአብና ከወልድ የመንፈስ ቅዱስ ሥርጸት አንድ

ድርጊት ነው። አንሰልም ፍልስፍናውን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ላይ ለመመሥረት ሞከረ፥ በተለይም ፦

አብ በስሜ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ (ዮሐ. 14፥26) እና

ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ (ዮሐ. 15፥26)።

የሚሉትን ጥቅሶች አያያዛቸው። ምሥራቃውያን በዮሐንስ 15፥26 የሚገኘውን ሐረግ «... እርሱም ከአብ የሚወጣ» በሚለው ሐረግ ላይ አሳባቸውን ለማጽናት ቢጥሩም፥ አንሰልም እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በአንድነት አብ ለወልድ፥ ወልድ ደግሞ ለአብ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልኩ ያሳያሉ ሲል አስተምሯል። ምሥራቃውያን ግን በምግባራዊ ሦስትነትና በህላዌያዊ ሦስትነት መሥረጽ መካከል ልዩነት አለ ይላሉ (11)።

አኩናስ ስለ ቅድስት ሥላሴ ትምህርቱን ሲጀምር እንደሚከተለው አስተማረ። የሰው አመክንዮታዊ አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ህልውና አንድነት ማስተዋል ሲችል፥ በሦስቱ አካላት መካከል ያለው ግንኙነት በእግዚአብሔር ሲገለጥ ብቻ ይታወቃል። በአመክንዮት የምናውቀው አምላክ በማስተዋል ወይም በፈቃዱ ይሠራል። ከአብ እርሱን የሚመስለው ወልድ በጥበቡ ተገኘ። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሠረጸ ቢሆንም፥ ፍጹም አምላክ ነው። በዚህ ምክንያት በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ልዩነት አለ፤ ሆኖም የመንፈስ ቅዱስን ግንኙነት አስመልክቶ አኩናስ የነበረው አስተሳሰብ ወደ አውግስጢኖስ አስተሳሰብ ይጠጋል (12)።

ስለ ቅድስት ሥላሴ የአንሰልምንና የአኩናስን ትምህርት ስንመለከት፥ ፍልስፍና የበዛበት ሊመስለን ይችላል። እነዚህ ሊቃውንት ከሦስቱ አካላት ጋር በሕይወታቸው እንዴት እንደተገናኙ ለማስተዋል ይከብዳል። በሦስቱ አካላዊነት ላይ ሳይሆን በህልውናቸውና በባሕርያቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ ሊመስለንም ይችላል። በካቶሊኮችና በአንዳንድ ፕሮቴስታንቶች ዘንድ አንዳንዶች የአኩናስን ትምህርት ሳይለቁ አሳቡ የበለጠ እንዲስፋፋ ለማድረግ ሞክረዋልና የአኩናስ ትምህርት የወደፊት ዕድገት ቢያሳይ አያስገርምም (13)።

7. ዮሐንስ ካልቪን (1509-1564)

ካልቪን ስለ ቅድስት ሥላሴ ሲጽፍ፥ የአውግስጢኖስ ትምህርት ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኘው መሰከረ፤ አበውም በዚህ ርእስ ላይ የሰጡትን ዋና ትምህርት ተቀበለ። በዘመኑ የተነሣውን ልዩ ልዩ ስሕተትም ተቃወመ። ይህንም ሲያደርግ፥ ከካቶሊኮችና ከአበው የሚለይበትን በሚከተሉት አራት ነጥቦች ማየት እንችላለን (14)፤ ሌሎች የተሐድሶ መሪዎች ግን በእነዚህ ነጥቦች ከእርሱ ጋር ይስማሙ ነበር።

ሀ) በትምህርተ መለኮት የእግዚአብሔር ህልውና ዋና ጥናት መሆን የለበትም። የተሐድሶ ተከታዮች የእግዚአብሔር ህልውና እንዳለ አልካዱም። ሆኖም እግዚአብሔር ስለ ህልውና ብዙ አይናገርም፤ ምክንያቱም ሰው ሌላ ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ይፈልጋል። አንዳንዶች ሰው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚሆነው፥ በልዩ ልዩ የተመሰጦ ሁኔታ በመግባት ነው ብለው ያስተምሩ ነበር። እነካልቪን ግን ለክርስቲያን መንፈሳዊ ኑሮ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው በቂ በመሆን ላይ አተኮሩ።

ለ) ሦስቱ አካላት በማናቸውም ደረጃ ፍጹም እኩል ናቸው። ይህ ከጥንት የመጣ ትምህርት ነበረ፤ በቅዱስ አትናቴዎስ የሃይማኖት ሥርዐት፥ «በዚችም ሦስትነት መቅደም መከታተል የለም፤ ከባልንጀራውም የሚበልጥና የሚያንስ የለም» ይላልና (15)። ሆኖም በካልቪን ዘመን ሌሎች አብ የአምላክነት መነሻ መሆኑንና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብና የወልድ አንድነት ትስስር እንደሆነ በማመናቸው ይህን እኩልነት

አቃልሎት ነበር። ካልቪን፥ የሦስቱ አምላካዊ አንድነት የሚታየው አካላዊነት በሌለው ህልውና በመሳተፋቸው ሳይሆን፥ ውሳጣዊ የእርስ በርስ ኅብረትና ህላዌ ስላላቸው መሆኑን አስተማረ። በሌላ አነጋገር አንድነታቸው በህላዌ ደረጃ ሳይሆን በአካልነት ነው።

ሐ) ሰው አንዱን አካል በማወቅ ሦስቱን ያውቃል። ካልቪን፥ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ልብ ሁሉ መኖር የጀመረው ከበዐለ ኀምሳ ቀን በኋላ መሆኑን አስተማረ። ከዚህም የተነሣ ምእመናን ስለ ሦስቱ አካላት፥ ስለ ምግባራቸውና እርስ በርስ ስላላቸው ግንኙነት ማሰብ ችለዋል። ከዚህም ቀጥሎ ሥላሴ በአንድነት ፈጣሪ፥ አዳኝና የሚቀድስ መሆኑን አስተውለዋል። በዚህ ምክንያት አብ በማንሣሣቱ፥ ወልድ በማደራጀቱና መንፈስ ቅዱስ ኀይልን በመስጠቱ የእያንዳንዱን ምግባር ለይተን ማወቅ እንችላለን። በዚህ ምግባር እንደ አብና እንደ ወልድ የመንፈስ ቅዱስ አካልነት ይታያል።

ካልቪን ከሦስቱ አካላት እያንዳንዱ ራሱን የቻለ ነው (AUTOTHEOS) በማለቱ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በግዴታ ሳይሆን በውዴታ መሆኑን በአጽንዖት አሳሰበ። ይህ ነጻነት ግን ወደ መቀዋወም ወይም ወደ ትርምስ ሊመራ አይችልም፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር አንድ ፈቃድ ብቻ አለ፤ ይህም ፈቃድ በውሳጣዊ የእርስ በርስ ፍቅር ይገዛል። ስለዚህ ሰው ይህን ከተረዳ በሦስት አማልክት ትምህርት ወይም በሰባልዮሳዊ ስሕተት አይጠመድም።

እውነት ነው፤ ካልቪን የአብን ቀዳሚነት ሲያብራራ የወልድ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ነው ይላል፤ ሆኖም ወልድ የሚሆነውንና የሚያደርገውን ሁሉ በአብ ዐውድ መረዳት አለበት፤ ምክንያቱም ወልድ ራሱን የሚያየው በዚህ መሠረት ነው፤ በዚህ ሁኔታ ወልድ ከዘለዓለም ያለ እንጂ በአብ የተደገፈ አይደለም። አብ ራሱን የቻለ እንደ መሆኑ ሁሉ፥ ወልድም ራሱን የቻለ ነው።

መ) ሰው በእግዚአብሔር መልክ ቢፈጠርም በሥላሴ ወይም በክርስቶስ ምሳሌ መተርጐም ተገቢ አይደለም። ይህ አባባል የአውግስጢኖስ ነበረ፤ የግሪክ አባቶችና ከአውግስጢኖስ በፊት የነበሩ የላቲን አባቶችም ይህ ዐይነት አስተሳሰብ ነበራቸው። ካልቪን የአበውን አሳቦች ባይቀበልም፥ በሰው አፈጣጠር የእግዚአብሔር ምሳሌ እንዴት እንደሆነ ለመግለጥ ሲሞክር አጥጋቢ ማብራሪያ አልሰጠም። የእግዚአብሔር ምሳሌ በሰው የሚታየው «ከእንስሳት ሁሉ ሰው በሚበልጥባቸው ሁሉ» መሆኑን ጽፏል። ይህም በተለይ የሰውን አመክንዮትና ፈቃድ ወይም የሰውን «ነፍስ» የሚመለከት እንደሆነ አየ። ይህ በቂ ማብራሪያ ባይሆንም፥ ካልቪን የሰውን በእግዚአብሔር ምሳሌ መፈጠር የተረዳው በተለይ እግዚአብሔርን ከማወቅ ችሎታው አንጻር ወይም በትምህርተ መለኮት አገላለጥ ሰው አካልነት ያለው ከመሆኑ አኳያ ነው።

ሰው በክርስቶስ መልክ እንዳልተፈጠረ ግልጽ መሆኑ ክርስቲያን የሚያጋጥመውን በሥላሴያዊ መንገድ ማስተዋል እንዲችል በር ከፈተ፤ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት በጸጋ መግባቱንም በተለይ እንዲያውቅ አደረገ።

8. ካርል ባርት (1886-1968)

ከዚህ በላይ እንዳየነው ከጥንት ጀምሮ በነበሩ ሁለት ትውፊቶች (የምሥራቅና የምዕራብ) መሠረት የእግዚአብሔር አንድነት የሚገለጠው በአብ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ነው።

ሰው ነገረ መለኮትን በትክክል ሲያስተምር የዘመኑን ዐውድ ተመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስን ያብራራል። በባርት ዘመን የነበሩ ሊበራል መምህራን ኢየሱስ የክርስትና ሃይማኖት እምብርት እንደሆነ ቢያምኑም፥ እርሱ ብዙ ስጦታ ያለው የይሁዳ ሰው ብቻ

መሆኑን ያስተምሩ ነበር። ባርት ግን ክርስቶስ የክርስትና ማዕከል መሆኑን በመቀበል እርሱ ለሰው ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር አስተርእዮ መሆኑን ዐወጀ (16)።

ባርት የአንሰልምን አሳብ በብዙ በኩል ተከተለ። አንሰልም በመስቀሉ ላይ የክርስቶስ መሥዋዕት በሥላሴ ውስጥ የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን አስተዋለ። ወልድ ለአብ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ፤ መንፈስ ቅዱስም በክርስቲያን ኑሮ መሥዋዕቱን ሕያው አደረገው። ስለዚህ በወልድ ትሥጉታዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ጥበብ፥ ኀይልና ፍቅር ይታያሉ። በዚህ ትምህርት ላይ በማተኰር የክርስቶስ ስፍራ በተለይ በስብከት ምን ስፍራ ሊኖረው እንደሚገባ አሳይቷል።

ባርት በዚህ ዐይነት ለትምህርተ ሥላሴ የክርስቶስን ሚና ከፍ ከፍ በማድረጉ ሳንደሰት አንቀርም። ሆኖም በሁለት ነገሮች ልናመነታ ይገባናል። አንደኛ፥ ኢየሱስ ሰዎችን ወደ ራሱ እንዲመለከቱ ቢያደርግም፥ አብን ደግሞ እንዲመለከቱ አድርጓል፤ በተለይ ለአባታችን እንድንጸልይ አስተማረን። ከዚህም ቀጥሎ መንፈስ ቅዱስ «ሌላ አጽናኝ» በመሆኑ በክርስቲያን ሕይወት ትልቅ አገልግሎት ይኖረዋል። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር በክርስቶስ ብቻ ከተገለጠ፥ ስለ ክርስቶስ እግዚአብሔርን አስመልክቶ የተባለው ሁሉ እውነት ነው። ባርት ይህን አሳብ ተከታትሎ አላሳደገውም፤ ከደቀ መዛሙርቱ አንዳንዶቹ ግን አሳቡን አበልጽገው በመጨረሻ የክርስቶስን ስቅለት የእግዚአብሔር ሞት አድርገው ተመለከቱት።

9. የሥላሴ ትምህርት በኢትዮጵያ፤ የሦስት መለኮት ትምህርት

አንድ ሊቅ ስለዚህ አስተሳሰብ እንደሚከተለው ጽፈዋል ፡-

በትምህርተ መለኮት ረገድ «መለኮት በአካል ሦስት ነው» በማለት የሚያስተምሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት መኖራቸው ግልጥ ነው። እነዚህ ሊቃውንት ቤተ ጣዕመ ክርስቶስ በመባል ይታወቃሉ። ጣዕመ ክርስቶስ በ1823 ዓ.ም. የዋልድባ ገዳም አበ ምኔት የነበሩ ናቸው። መለኮት በአካል ሦስት ነው የሚለው ትምህርት ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተከሠተ ቢሆንም፥ በግልጥ ያስፋፉት አባ ጣዕመ ክርስቶስ ናቸው። ይህን የእርሳቸውን ትምህርት የተከተሉ ሁሉም «ቤተ ጣዕመ ክርስቶስ» ተብለዋል። የጣዕመ ክርስቶስ ወገኖች ማለት ነው።

እነዚህ ወገኖች እንደዚህ ለማስተማር የተነሡበትን ምክንያት ሲገልጡ እንዲህ ይላሉ።

1. በአንዳንድ የሊቃውንት መጽሐፍ «ሦስት መለኮት» የሚል ንባብ ይገኛል። «እስመ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሠለስቱ ትልቁ መለኮቱ ፡- የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መለኮት ቍጥር ሦስት ነው» (ሳዊርያኖስ እስትንቡእ ዘቁርሎስ)።

2. መለኮት አንድ ከሆነ፥ ይህንም ሦስቱ አካላት ከተገናዘቡት (ካላቸው)፥ እግዚአብሔር ወልድ ሰው በሆነ ጊዜ ሦስቱ አካላት ሁሉ ሰው ሆኑ ያሰኛል በማለት የሚከተለውን ሐተታ ያቀርባሉ።

«ወልድ በተለየ አካሉ ሰው በሆነ ጊዜ በፈቃድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ፥ የአብና የመንፈስ ቅዱስም መለኮት ሰው ሳይሆን የወልድ መለኮት (ባሕርይ) ሰው ሆነ ይባላል። አካሉ ሰው ሆነ ባሕርዩ ግን ሰው አልሆነም አይባልምና። ለዚህም የሚከተለውን ይጠቅሳሉ ፡- «ኢተዋሐደ በመንፈቀ ህላዌ ማለት ባሕርዩን ከፍሎ አልተዋሐደም» (ኤፍሬም ሃይ. አበ. ም. 47 ክ.5 ቍ32)።

እንደገናም «መለኮትን በአካል ሦስት ስንል፥ መለኮት በሥጋ ሞተ ካልን አንድ አካል፥ አንድ ገጽ ከሚሉ ሰዎች ጋር አንድ እንሆናለን። ሦስቱ አካላትም ሞቱ ማለት ይሆንብናል። ስለዚህ መለኮት በሥጋ ሞተ የምንለው ከሦስቱ የአንዱ የወልድን አካል መለኮት ነው ...» ይላሉ።

እነዚህ ወገኖች መለኮት ሦስት ነው ማለታቸው ዘጠኝ መለኮት ወይም ዘጠኝ አካላት እንደሚያሰኝባቸው በመገንዘብ «መለኮት በአካል ሦስት ነው» ካልተባለ በቀር «መለኮት ሦስት ነው» ማለት ብቻ የዮሐንስ ተዓቃቢ እምነት ይሆናል በማለት መንገድ ይዘጋሉ።

3. በተጨማሪም ሦስት መለኮት ባዮች የመለኮትን ትርጉም ከላይኛው አሳባቸው በመለወጥ መለኮት ማለት አካል ማለት ነው ይሉና «ወላዲ መለኮት፥ ተወላዲ መለኮት፥ ሠራፂ መለኮት» በማለት የመለኮትን ሦስትነት በሌላ ዘዴ ይገልጣሉ። ለዚህም የሚከተለውን ንባብ ከሊቃውንት ይጠቅሳሉ :-

«መለኮትስ አካላት ናቸው።» (ባስልዮስ ዘአንጾኪያ ሃይ. አበ. ም. 96 ክ.1 ቍ.5)፤

«አካላትም መለኮት ናቸው።» (አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ሃይ. አበ. ም.26 ክ.5 ቍ.3)፤

«መለኮትስ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ናቸው» (ሕርያቆስ ቅዳሴ ማርያም ቍ.57)።

ይህንም አባባላቸውን «አካል ከመለኮት፥ መለኮትም ከአካል ስለማይለይ መለኮት በአካል ሦስት ነው፤ መለኮትም አካል ማለት ነው። አካላትም በመለኮት አንድ ናቸው ማለት በዕሪና (እኩልነት) በህልውናና በፈቃድ፥ በባሕርይና በግብር አንድ ናቸው ማለት ነው።» ብለው ይደመድማሉ። (ምሥጢረ ሥላሴ 3 መለኮት በሚሉ ወገኖች የተጻፈ ያልታተመ ገጽ 1-19። ትርጓሜ ትሥልስት ገጽ 20-26።)

ይሁን እንጂ የእነዚህ ወገኖች ስለ መለኮት ያላቸው ግንዛቤ ትክክል ስላይደለ ከሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት የሚከተለው ትችትና መልስ ተሰጥቷል። መልሱም የሚከተለው ነው :-

«ወላዲ መለኮት፥ ተወላዲ መለኮት፥ ሠራፂ መለኮት ማለት አይገባም። ምንም ቢሆን ወላዲው ተወላዲና ሠራፂ፥ ተወላዲውም ወላዲና ሠራፂ፥ ሠራፂውም ወላዲና ተወላዲ ሊሆን የማይቻል ነው። አካላትን ልዩ የሚያሰኛቸው ይህ ነው። መለኮትን አካላት በሚለያዩበት ስም ጠርቶ ወላዲ መለኮት፥ ተወላዲ መለኮት፥ ሠራፂ መለኮት ማለት መለኮትን እንደ አካላት ሦስት ማለት እንደሆነ አስተዋይ ልቡና ያለው ሊረዳው ይችላል። እንዲህም ከሆነ ሊቃውንት በየአንቀጹ «እግዚአብሔር በአካላት ሦስት ነው፤ በመለኮትም አንድ ነው» ያሉት ንባብ ሐሰት ይሆናል።»

«መለኮት በራሱ ወላዲ፥ ተወላዲ፥ ሠራፂም ከተባለ፥ ሦስት በመሆኑ የመንገዱ ጥርጊያ ወደ ዮሐንስ ተዓቃቢ ቤት የሚያገባ መሆኑ አያጠራጥርም።» ስለ ዮሐንስ ተዓቃቢ በሃይማኖተ አበው መጽሐፍ ምዕራፍ 91 ክፍል 1 ቍጥር 11 ተገልጧል።

«ሊቃውንት ሦስቱን አካላት መለኮት ብለው መናገራቸው መለኮት በአካል ልዩ ነው ብለው አይደለም። ነገር ግን አንዱ መለኮት በሦስቱ አካላት ህልው (የባሕርይ ገንዘብ) ነው ብለው ነው። ይህንም ሲያስረዳ የአንጾኪያው ባስልዮስ የሚከተለውን ተናግሯል፤ «እኔ እግዚአብሔር ባልሁ ጊዜ ስለ አብ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ እናገራለሁ። የሦስቱ መለኮት አንድ ነውና። ሦስቱም በመለኮት አንድ ናቸውና ...»

(ሃይ. አበ. ም. 96 ክ.1 ቍ.6) ሦስቱ አካላት በክብር ዙፋን ያሉ ፍጹማን ናቸው፤ በአንድ መለኮትም የተገናዘቡ ናቸው።» (ኢግናጢዮስ ሃይ. አበ. ም. 11 ክ.1 ቍ.8) ...ወዘተ።

መለኮት ከአካላት ጋር በሦስት የሚከፈል ከሆነ፥ አንድ ልብ፥ አንድ ቃል፥ አንድ እስትንፋስም መሆን የለም። ይህም ከሌለ፥ በአብ ለባውያን (አሳቢዎች)፥ በወልድ ነባብያን (ተናጋሪዎች)፥ በመንፈስ ቅዱስም ሕያዋን መባል አይገኝም። ለእየራሳቸው ልብ፥ ቃልና እስትንፋስ አላቸው በማለት እንደ ዮሐንስ ተዓቃቢ ዘጠኝ መለኮት ማለት ያሰኛል። ዮሐንስ ተዓቃቢ ከዚህ የተለየ አልተናገረምና።

መለኮት በአካል ሦስት ነው ማለት ሦስት ልብ፥ ሦስት ቃል፥ ሦስት እስትንፋስ ማለትን ያስከትላል። ይህ ደግሞ ዘጠኝ መለኮት ወይም ዘጠኝ አካላት ወደ ማለት ያደርሳል። ስለሆነም :- «መለኮት በአካል ሦስት ነው ማለት ከሚያመጣው ስሕተት መጠበቅ» ያስፈልጋል። ፍኖተ እግዚአብሔር ዘአለቃ ኀሩይ ያልታተመ አንቀጽ 3።

ይህን ትምህርት በዚህ መጽሐፍ ከተጻፈው ጋር ለማዛመድ ስንሞክር ሁለት ነገር ማተት ያስፈልጋል። መጀመሪያ አንድ አነስተኛ ነገር አለ፤ ይኸውም ስለ ቅድስት ሥላሴ ምሳሌዎችን ለማግኘት ስንፈልግ ከመጠን በላይ ምሳሌውን ብንጠቀምበት ወደ አሳብ ጕድጓድ እንወድቃለን። እዚህ ላይ ልብ፥ ቃልና እስትንፋስ ሥላሴን ለማስረዳት በምሳሌነት በመጠቀም ብዙ ችግር ተፈጥሯል። ስለዚህ ምሳሌ በዚህ ምዕራፍ ክፍል ሐ2ሐ እናትታለን።

ከዘጠኝ መለኮት ትምህርት የተነሣ በተለይ የጣዕመ ክርስቶስ ወገኖች በእግዚአብሔር ዘንድ አንድነት ምሥጢራዊነት ያለው መሆኑን ባለማስተዋላቸው ነው። ስለ እግዚአብሔር አንድነት በተለይ በምዕራፍ 25 መ2 እና 26ለ አትተናል። ይህን በትክክል ቢረዱ ኖሮ ሦስት አካላት ካሉ ሦስት ልዩ ዐይነት መለኮቶች ወይም ሦስት ዐይነት ባሕርያት አሉ አይሉም ነበር። ትክክለኛ ትምህርት እግዚአብሔር ወልድ ፍጹም መለኮትና አምላካዊ ባሕርይ ሲኖሩት፥ እንደ ግል አካላዊነት (ወልድነት እንዳለው) ሰው ሆነ። ይህ ምሥጢር መሆኑን አንክድም፤ ምሥጢሩን በትክክለኛ ቦታ ማስቀመጥና በዚያው መተው አለብን።

## ለ) ትምህርተ ሥላሴ በሃይማኖት ሥርዐቶች

ስለ ምሥጢረ ሥላሴና ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት የሚገባውን ትምህርት ለመግለጥና ለመወሰን ሦስት የታወቁ የሃይማኖት ሥርዐቶች ተደነገጉ። እነርሱም በተለይ ከሰባልዮስና ከአርዮስ ስሕተቶች የተነሣ የተደነገጉ ናቸው። እነዚህ የሃይማኖት ሥርዐቶች በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ በመሆናቸው፥ በየዘመኑ በልዩ ልዩ ሊቃውንት በአማርኛ ሲተረጐሙ በልዩ ልዩ ትርጕም የቃል ልዩነት ይታይባቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ምንም እንኳ ትምህርተ ሥላሴ ቢጠናም፥ የሃይማኖት ሥርዐቶችን በሙሉ ለማቅረብ ምቹ እንደሆነ እንገምታለን።

### 1. የሐዋርያት ሥርዐተ ሃይማኖት

ይህ የሃይማኖት ሥርዐት በሐዋርያት ባይጻፍም፥ ትምህርታቸውን ያዘለ እንደሆነ ይታመናል። በሮም ከ250 ዓ.ም. በፊት ለተጠመቁ ምእመናን በመጀመሪያ በግሪክ ቋንቋ ተዘጋጀ፤ ቈይቶም ወደ ላቲን ተተረጐመ፤ በየዘመኑ እስከ ስምንት መቶ ዓመታት ድረስ በልዩ ልዩ አገር አንዳንድ ሐረጎች እየተጨመሩበት ቀስ በቀስ እየረዘመ ሄደ። ሥርዐቱ በምሥራቃውያን ዘንድ ቢታወቅም፥ በተለይ ምዕራባውያን ለትምህርትና ለአምልኮ ተጠቅመውበታል። ይዘቱ ሥላሴያዊ ሲሆን፥ የክርስቶስን ሥራ ይዘረዝራል (17)።

የሐዋርያት ሥርዐተ ሃይማኖት :-

ስለ አብ

ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፥ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ስለ ወልድ

በአንድ ልጁም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ፥ ከድንግል ማርያም የተወለደ፥ በጲላጦስ ጴንጤናዊ ዘመን መከራ የተቀበለ፥ የተሰቀለ፥ የሞተ፥ የተቀበረ፥ ወደ ሲኦልም የወረደ፥ በሦስተኛው ቀንም ከሙታን የተነሣ፥ ወደ ሰማይም ያረገ፥ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ፥ ከዚያም በሕያውንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ እናምናለን።

ስለ መንፈስ ቅዱስ

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፥ በአንዲት ቅድስት ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን፥ በቅዱሳን አንድነት፥ በኀጢአትም ስርየት፥ በሥጋም ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። አሜን።

2. የኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት

በ325 ዓ.ም. ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ጳጳሳት ስለ አርዮስ ትምህርት ርምጃ ለመውሰድ በኒቅያ (በቢታንያ አውራጃ፥ ፋርስ አገር) ተሰበሰቡ። ቅዱስ አትናቴዎስ (ሀ3 ይመ.) ጉባኤው ላይ ነበረ። ጉባኤውም የኒቅያን ሥርዐተ ሃይማኖት ደነገገ። ከዚያም በኋላ ይህ የሃይማኖት ሥርዐት በቍስጥንጥንያው ጉባኤም ሆነ በሌላ ዘንድ አንዳንድ ለውጦች ተደርገው በ451 ዓ.ም. በኬልቄዶን ጉባኤ የመቶ አምሳ አበው የእምነት አንቀጽ ሆኖ ተነበበ፤ ይህ የተነበበው የእምነት አንቀጽ ዛሬ የኒቅያ ሃይማኖት ሥርዐት እንደሆነ ይታወቃል፤ ለቤተ ክርስቲያን አምልኮትና ትምህርት ጥቅም እየሰጠ ይገኛል። «እና ከወልድ» የሚለው ሐረግ (ሀ5 ይመ.) በኋላ በምዕራባውያን ተጨምሯል (18)። ይህ ሥርዐተ ሃይማኖት የአብና የወልድ መለኮት አንድ መሆኑን በመግለጹ የአርዮስን ትምህርት በግልጥ ይቃወማል።

የኒቅያ ሥርዐተ ሃይማኖት በአማርኛ :-

ስለ አብ

ሁሉን በሚገዛ ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፥ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ስለ ወልድ

ዓለም ሳይፈጠር፥ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን፥ በአንድ ጌታ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን። እርሱም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ፥ በመለኮቱ ከአብ ጋር አንድ የሆነ፥ ሁሉ በእርሱ የሆነ፥ በሰማይና በምድር ካለው ሁሉ ያለ እርሱ ምንም የሆነ የሌለ፥ ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛንም ስለ ማዳን ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስም ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ለበሰ፤ ሰውም ሆነ፤ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ፤ መከራን ተቀበለ፤ ሞተ፤ ተቀበረም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በክብርም ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ በጌትነት ይመጣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ

ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት በሚሰገድለትና በሚመሰገን፥ ጌታ፥ ሕይወት ሰጭ በሚሆን፥ ከአብ «እና ከወልድ» በሠረፀ፥ በነቢያትም በተናገረ፥ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።

በሁሉም ዘንድ በምትሆን፥ ሐዋርያት በሰበሰቧት፥ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

ለኀጢአትም ስርየት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። የሙታን ትንሣኤንና የሚመጣውን ዓለም ሕይወት በተስፋ እንጠባበቃለን። አሜን።

3. የቅዱስ አትናቴዎስ ሥርዐተ ሃይማኖት

ይህ የሃይማኖት ሥርዐት ከአትናቴዎስ ሞት በኋላ ቢጻፍም የአትናቴዎስን አሳብ ይከተላል። ማን እንደጻፈው አይታወቅም። በመጀመሪያ የተጻፈው በላቲን ቋንቋ ሲሆን በምዕራባውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ብዙ ጥቅም ሰጥቷል። የሃይማኖት ሥርዐቱ ከላቲን ወደ ግሪክ ተተርጒሟል፤ ትርጒሙ ግን የFILIOQUE ሐረግን አልያዘም። ትምህረተ ሥላሴን በጥሩ አኳኋን ይገልጣል፤ የአርዮስንና የሰባልዮስን ስሕተቶችም ይቃወማል(19)።

የቅዱስ አትናቴዎስ ሥርዐተ ሃይማኖት ፡-

ለመዳን ፈቃደኛነት ያለው ሰው ሁሉ ይህን በሁሉ ዘንድ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የምትከተለውን ሃይማኖት ይጠብቅ ዘንድ ይገባዋል። ስለዚህም ደኅንነትን እንዳያጣ ይህን እምነት መጠበቅ ያስፈልገዋል።

በሁሉ ዘንድ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትም ፡- አካላትን ሳንደባልቅና ህላዌን ሳንከፍል አንዱን አምላክ በሦስትነት፥ ሦስትነትንም በአንድነት እናመልክ ዘንድ ነው። አንዱ አካል የአብ ሲሆን፥ ሁለተኛው የወልድ፥ ሦስተኛውም የመንፈስ ቅዱስ ነው። ነገር ግን የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንዲት ናት። ክብራቸውም የተካከለ ነው። ግርማቸውም የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናት።

አብ እንዳለ እንዲሁም ወልድ አለ መንፈስ ቅዱስም አለ። አብ አልተፈጠረም፤ ወልድም አልተፈጠረም፤ መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም። አብ አይወሰንም፤ ወልድም አይወሰንም፤ መንፈስ ቅዱስም አይወሰንም። አብ ዘለዓለማዊ ነው፤ ወልድም ዘለዓለማዊ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ዘለዓለማዊ ነው። ነገር ግን በዘለዓለማዊነት ያለ አንድ ነው እንጂ ሦስት ናቸው አንልም።

እንዲሁም የማንወስነውና ያልተፈጠረ አንድ ነው እንጂ የማንወስናቸውና ያልተፈጠሩ ሦስት ናቸው አንልም። እንደዚሁም አብ ሁሉን ቻይ ነው፤ ወልድም ሁሉን ቻይ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን ቻይ ነው። ነገር ግን ሁሉን የሚችል አንድ ነው እንላለን እንጂ ሦስት ሁሉን ቻዮች አንልም።

እንደዚሁም አብ አምላክ ነው፤ ወልድም አምላክ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው፤ ዳሩ ግን አንድ አምላክ ነው እንጂ ሦስት አማልክት አንልም።

እንደዚሁም አብ ጌታ ነው፤ ወልድም ጌታ ነው፤ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው፤ ስለሆነም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አንልም። በክርስትና እውነትነት እንደምንለው ፡- አካል ሁሉ እያንዳንዱ በየራሱ አምላክና ጌታ ሆኖ ሳለ፤ ሦስት አማልክትና ሦስት ጌቶች ከማለት የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን አምልኮ እምነት ትከለክለናለች።

አብ ከማንም አልተሠራም፤ አልተፈጠረም፤ አልተወለደም፤ ወልድም በአብ ነው፤ ስለሆነም ተወልዶ ነው እንጂ ተሠርቶ ወይንም ተፈጥሮ አይደለም። መንፈስ ቅዱስም በአብ ነው። ዳሩ ግን ሠርፆ እንጂ ተሠርቶ ወይንም ተፈጥሮ ወይም ተወልዶ አይደለም።

እንግዲህ አንድ አብ አለ እንጂ ሦስት አባቶች የሉም፤ አንድ ልጅ አለ እንጂ ሦስት ልጆች (ወልዶች) የሉም፤ አንድ መንፈስ ቅዱስ አለ እንጂ ሦስት መንፈስ ቅዱሶች የሉም። በዚችም ሦስትነት መቅደም መከታተል የለም፤ ከባልንጀራውም የሚበልጥና የሚያንስ የለም። ሦስቱ አካሎቻቸው እየራሳቸው የአንዲት ዘለዓለማዊነት ናቸው። እየራሳቸውም የተካከሉ ናቸው። እንግዲያውስ እንደተባለው ሁሉ ሥላሴን በአንድነት፥ አንድነትንም በሥላሴ ማመን ይገባል።

መዳንን የሚሻ በሥላሴ እንደዚሁ ያስብ።

ዳግም ስለ ዘለዓለም ሕይወቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትሥጉት በሚገባ ያምን ዘንድ ለሰው ያስፈልገዋል።

ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችን ስትባል ይህንኑ ማመናችን ማለት እንደ መሆኗ፥ ወልደ እግዚአብሔር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና ሰው ነው። እምቅድመ ዓለም ከአብ ህላዌ በመወለዱ አምላክ ነው፤ ድኅረ ዓለምም ከእናቱ ህላዌ በመወለዱ ሰው ነው። በሰው ነፍስና ሥጋ ፐዩቅ (ፍጹም) ሰው ሆኖ ፍጹም አምላክ ነው። በመለኮቱም ከአብ ጋር አንድ ሲሆን የባሪያውን መልክ ወሰደ። ዳሩ ግን አምላክና ሰው እንደ መሆኑ አንድ ክርስቶስ ነው እንጂ እርሱ ሁለት አይደለም። አንድ ነው ግን መለኮቱ ሰውነትን በመገንዘብ ነው እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ በመለወጥ አይደለም። ፈጽሞ የተዋሐደ ስለሆነ በባሕርይ መደባለቅ ሳይሆን በአካል መዋሐድ ነው። ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደሚያሰኝ ሁሉ አምላክና ሰው የሆነ አንድ ክርስቶስ ነው።

እርሱም እኛን ለማዳን መከራን ተቀበለ፤ ወደ ሲኦልም ወረደ። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ ወደ ሰማይም ዐረገ፤ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ፤ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድም ከዚያ ይመለሳል።

እርሱም በሚመጣበት ጊዜ ሰው ሁሉ በሥጋው ይነሣል። ባደረገውም ሥራ ሁሉ ይቈጣጠረዋል። መልካም የሠሩ ወደ ዘለዓለም ሕይወት፥ ክፉ የሠሩም ወደ ዘለዓለም እሳት ይገባሉ።

ከሁሉ በላይ የምትሆን የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ይህች ናት፤ ያላመናት ሰውም ይድን ዘንድ አይቻለውም።

ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን፤ በመጀመሪያ እንደነበረ አሁንም እንዳለ፤ ለዘወትርም እንደሚኖር ለዘለዓለም፤ አሜን።

## ሐ) የቅድስት ሥላሴ ምሳሌዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅድስት ሥላሴ አንድም ምሳሌ ስለማይገኝ ምሳሌ ምንም አይጠቅምም የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ሌሎች ግን ቅድስት ሥላሴ ለብቻው ቢሆንም፥ ልዩ ልዩ ምሳሌዎች አንድ አሳብን ስለ ቅድስት ሥላሴ ማብራራት ይችላሉና በጥንቃቄ ብንጠቀምባቸው፥ ሰውን እንዲያስተውል ሊረዱት ይችላሉ ይላሉ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ልዩ ልዩ ምሳሌዎች ይገኛሉና ጥቅማቸውንና ጉድለታቸውን በዐጭሩ ማየት ይገባናል። ምሳሌዎችን በሦስት አርእስት ከፍለን ማየት እንችላለን።

1) ከግዑዙ ዓለም፥ ከተክልና ከእንስሳት የሚገኙ ምሳሌዎች

ሀ) ዕንቍላል፤ አስኳል፥ ውሃና ቅርፊት አሉት። እነዚህ ሦስት የዕንቍላል ክፍሎች አይመሳሰሉም፤ የአካላዊነት ጠባይ የላቸውም። ሆኖም ዕንቍላል ውስብስብነት ያለውን አንድነት ሊያሳይ ይችል ይሆናል።

ለ) ዛፍ፤ ሥር፥ ግንድና ቅርንጫፍ አሉት። ሦስቱ ዕንጨትነት ቢኖራቸውም፥ ሦስት ክፍሎች ናቸው፤ አንዱ ክፍል ዛፉ ሁሉ አይደለም፤ የአካላዊነት ጠባይ የላቸውም።

ሐ) ምንጭ፥ ፈሳሽና ሐይቅ ውሃን በሦስት ሁኔታዎች ያሳያሉ፤ ሆኖም የአካላዊነት ጠባይ የላቸውም። ለሰባልዮስ የስሕተት ትምህርት ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ።

መ) ፀሐይ ብርሃንና ሙቀት ትሰጣለች። እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎች ከአንድ መነሻ ወጥተው ይገኛሉ። በዚህ ምክንያት በአንድ በኩል ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ የመውጣታቸው ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ብርሃንና ሙቀት አይመሳሰሉም፤ እያንዳንዱ ፀሐይንና ሌላውን አይይዝም፤ የአካላዊነት ጠባይ የላቸውምና ሙሉ የሥላሴ ምሳሌ ሊሆኑ አይችሉም።

2. በሰው ተፈጥሮ ላይ የተመሠረቱ ምሳሌዎች

ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ ስለተፈጠረ አንዳንዶች የሥላሴን ምሳሌዎች ከሰው ማግኘት ሞክረዋል።

ሀ) ሰው ገበሬ፥ ነጋዴና ቄስ ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ አንድ ሰው በሦስት ዐይነት ሥራ ራሱን ይገልጣል። ይህ እንደገና የሰባልዮስ የስሕተት ትምህርት ምሳሌ ሊሆን ይችላል!

ለ) በሰው ዘንድ አእምሮ፥ ስሜትና ፈቃድ አሉ። እነዚህ የአካላዊነት ክፍሎች ቢሆኑም፥ ከሦስቱ አንዱ ሰውን አሟልቶ አይይዝም፤ ደግሞም ሦስቱ ክፍሎች አይመሳሰሉም።

ሐ) ልቡና የአብ፥ ቃል የወልድ፥ እስትንፋስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች መሆናቸው በኢትዮጵያ የታወቀ የሥላሴ መግለጫ ነው። በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ «የእግዚአብሔር ቃል» እና «የእግዚአብሔር መንፈስ» ተብለው ይጠቀሳሉ። ሐዋርያው ዮሐንስ «ቃል ሥጋ ሆነ» በማለቱ ሁለተኛውን አካል አመለከተ። ሆኖም ከወንጌሉ መግቢያ በኋላ በዚህ ምሳሌ አይጠቀምም። ስለ «ቃል» የዮሐንስን አጠቃቀም «ትምህርተ ሥጋዌ» በሚለው 5ኛ ጥናት እንመለከተዋለን። መንፈስን የሚተረጕሙት የዕብራይስጥና የግሪክ ቃላት ነፋስ ወይም እስትንፋስ ተብለው ሊተረጐሙ ይችላሉ። ስለዚህ ከሌሎች ምሳሌዎች ይልቅ ለዚህ ምሳሌ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት እንዳለ ሊታሰብ ይችላል። ይህን ምሳሌ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ እንደሚከተለው አብራርተውታል (20) ፦ «ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አብ ልቡናቸው ነው፤ ለመንፈስ ቅዱስና ለአብም ወልድ ቃላቸው ነው፤ ለወልድና ለአብ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋሳቸው ነው፤ ማለት በአብ ልቡናነት 3ቱም ያስባሉ፤ በወልድ ቃልነት 3ቱም ይናገራሉ፤ በመንፈስ ቅዱስም እስትንፋስነት 3ቱም ሕያዋን ሆነው ይኖራሉና። ... እንዲህ ባለ መገነዛዘብ ቃልና እስትንፋስ ከልብ መቋረጥ እንደሌላቸው ወልድና መንፈስ ቅዱስም ከአብ መለየት የለባቸውም። በፈቃድ አንድ እንደ መሆናቸው ለመዓትም፥ ለምሕረትም በአንድ ይሠራሉ፤ ይፈጽማሉ ...»። ይህ ምሳሌ ከብዙ ሌሎች ምሳሌዎች የበለጠ የሥላሴን ሦስትነትና አንድነት ቢገልጥም፥ ፍጹም ምሳሌ ነው ማለት ይከብዳል። በምዕራፍ 26ሐ ስለ አብ፥ ስለ ወልድና ስለ

መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት በሰፊው ከተብራሩ ጥቅሶች ጋር ይህ አቀራረብ የሚስማማ አይደለም። በዐጭሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ፥ ከዘለዓለም የነበረው ቃል ከኢየሱስ ተለይቶ ወደ ሰማይ በመውጣት በአብ ስም ለራሱ «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሏል ወደሚል የተፋለሰ አሳብ ሰዎችን ሊያደርስ ይችላል። ሰው እንደዚህ ቢናገር «ቃል ሥጋ ሆነ» የሚለውን ምሥጢር አላፈረስህምን? ብለን እንጠይቀው። ክርስቶስም ለአብ ሲጸልይ ለራሱ የአብን ቃል መናገር የለበትምን? መጽሐፍ ቅዱስ አብ ተናገረ ወይም መንፈስ ቅዱስ ተናገረ ሲል ምን ትርጒም ይሰጣል? በሌላ አጠያየቅ በእግዚአብሔር ዘንድ «እኔ»፥ «አንተ»፥ «እርሱ» በማለት የሚያሳየው ግንኙነት እውነተኛ አካልነትና አካላዊነት አልጠፋምን? ብለን ከማሰብ እንድንቈጠብ አያደርጉም። እንግዲህ ልቡና፥ ቃልና እስትንፋስ ሦስትነትን በአንድነትና አንድነትን በሦስትነት በአንድ በኩል ቢያብራሩም፥ በሌላ በኩል ምሳሌው የሥላሴ አካላትን በአንድነት ከመግለጥ እጅግ የራቀ ምሳሌ እንደሆነ ማሳየት ይኖርብናል።

3. በፍቅር ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ምሳሌ

አብ ወዳጅ፥ ወልድ ተወዳጅና መንፈስ ቅዱስ በአብና በወልድ መካከል ያለ የፍቅራቸው ትስስር የሚለውን የአውግስጢኖስ ምሳሌ በ27 ሀ4 አትተናል። ምሳሌው የመንፈስ ቅዱስን አካልነትና አካላዊነት አይገልጥም። ደግሞም ሰው በፍቅር ላይ ተመሥርቶ ሥላሴን ለማብራራት ሲፈልግ፥ ሌሎች የባሕርይ መገለጫዎች በትምህርተ ሥላሴ ምን ዐይነት ስፍራ እንዳላቸው ማየት እጅግ ይከብዳል። ለበለጠ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በፍጥረት ስለሚታየው ሦስትነት በገጽ 272 የተጻፈውን ይመ.

## መ) አንዳንድ አስተያየቶች

ይህን ምዕራፍ ከመደምደማችን በፊት የተወሰኑ ነጥቦችን በዐጭሩ ማተት ተገቢ ነው።

1. ስለ ሥላሴ የሚጽፉ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ያጋጠማቸውን ለማስተዋልና ለመግለጥ ይሞክራሉ፤ በአምልኮታቸውም የተረዱትን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ። ስለዚህ አትናቴዎስና አውግስጢኖስ፥ ቀጳዶቅያውያንና አንሰልም፥ የደማስቆው ዮሐንስና አኩናስ፥ ካልቪንና ባርት ወደ አንዱ እግዚአብሔር ቀረቡ፤ እንደ ቋንቋቸው፥ እንደየዘመናቸው ሁኔታና እንደ ነበሯቸው ቃላት ምሥጢሩን ለማብራራት ሰፊ ጥረት አድርገዋል፤ እኛም የእነርሱ ባለ ዕዳዎች ነን፤ ዕዳችንን የምንከፍለውም ባለን ቋንቋና በምንጠቀምባቸው ቃላት ለትውልዳችን ምሥጢሩን በተራችን በትሕትና በማብራራት ነው። ይህን እንድንፈጽም እግዚአብሔር ይርዳን!

2. ስለ ጥንት ሰዎች፥ ስለ እነአርዮስና ስለ እነሰባልዮስ፥ እንደዚሁም ዛሬ ከጥንት የመጣውንና እውነትነቱ የተረጋገጠውን ትምህርት ስለማይቀበሉና ስለማያስተውሉ የምንሰጠው ፍርድ ጥንቃቄ የተመላበት መሆን ይኖርበታል። ትምህርታቸው ልክ አይደለም፤ ኑፋቄ አለበት፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይሰማ ርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ግን የሰውን ልብ ያውቃልና እርሱ ፈራጅ ነው። ብዙ ሰዎች ምንም እንኳ ልባቸው ወደ እግዚአብሔር ቢሆንም አገነዛዘባቸው የተስተካከለ አይደለም። ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ አካሄዳቸው የተዛባ ይሆናል። አንዳንዶች እልከኞች ይሆናሉና ከትዕቢት የተነሣ እውነቱን ሲነግሯቸው ለመቀበል ፈቃደኛ አይደሉም፤ ይልቁንም ይቃወሙታል። እንደነዚህ ዐይነቶችን ማውገዝና ከቤተ ክርስቲያን ማባረር ተገቢ ይሆናል፤ ይህን አሳብ «ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን» በተባለው በ8ኛው ትምህርት

በስፋት እንመረምራለን። ለጊዜው ግን ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ ቆስጠንጢኖስ ውሳኔውን ባለመቀበላቸው፥ የተወገዙትን ወደ ኢሊሪካም በማባረሩ፥ ለተወሰደው ክርስቲያናዊ የግፍ ርምጃ ሁሉ በር እንደከፈተ ማስተዋል አለብን። ይህ የክርስቶስ መንገድ አይደለም። ሐሰተኞችን በፍቅርና በመንፈሳዊ ኀይል እንጂ በስድብና በግፍ ወደ እውነት መምራት አዳጋች ነው(21)።

3. ትምህርተ ሥላሴን ለማብራራት ስንሞክር በአምስት አሳቦች መጀመር የሚቻል መሆኑን አይተናል። ከአንድነት ስንጀምር ወደ ሦስትነት ማለትም ወደ ሦስት አካላት የመድረስ ችግር አለ። ከእግዚአብሔር አብ ሲጀመር ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ መሆናቸውን ለማሳየት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተለያየ ችግር ተከሠተ። ሌሎች በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ጀምረዋል፤ ሆኖም ልዩ ልዩ ችግርን አስከትለዋል። በዚህ መጽሐፍ ከሦስቱ አካላት አንድነትና ኅብረት አንጻር ትምህርቱን ለማብራራት ሞክረናል። በእኛም አገላለጥ ቢሆን ችግር የለም ማለት አንችልም፤ ሥላሴ ምሥጢር ነውና።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብዙ ችግር የተፈጠረው በቃላት ትርጉም ምክንያት ነው። ይህን ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ለማብራራት የሞከርነው፥ ህላዌ፥ ህልውና፥ ባሕርይና አካል (እንደዚሁም አካልነት፥ አካላዊና አካላዊነት) በሚሉት ቃላት ነው። በግሪክና በላቲን ቋንቋዎች አበው በልዩ ልዩ ቃላት ተጠቅመዋል፤ ሆኖም የአካል ትርጉም ከዘመን ወደ ዘመን እየተለወጠና እየተሟላ እንደሄደ ሁሉ፥ የእነዚህም ቃላት አጠቃቀም ሁልጊዜ በጸሐፊዎች አገላለጥ አንድ አይደለም።

ከሃይማኖት ሥርዐቶች በኋላ በአብያተ ክርስቲያናት የሃይማኖት መግለጫዎች በተለይ ስለ ቅድስት ሥላሴ ብዙ አዲስ አሳብ አልመጣም።

ባለፉት መቶ ዓመታት ከሥነ ነፍስ ጥናትና በተለይ ከስግሙንድ ፍሮይድ ትምህርት የተነሣ ስለ አካልነት የሰው አስተሳሰብ እየተስፋፋ ሄዷልና ምናልባት ይህ ለሥላሴ ጥናት አዲስ አቅጣጫ ይከፍታል። ሆኖም ከጥንት ጀምሮ ከመጣው ትምህርት ብዙ የሚወጣ አይመስልም። ምኞቴና ጸሎቴ ከውሳጣዊ የእርስ በርስ አካልነት አስተሳሰብ የተነሣ፥ ምዕራባውያንና ምሥራቃውያን እየተቀራረቡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥርጸት ወደ ስምምነት እንዲደርሱ ነው።

## ማስታወሻ

(1) BYG ገጽ 193-198።

(2) እዚህ ላይ የተጻፈው በ ALISTER McGRATH ከተጻፈው ከ UNDERSTANDING DOCTRINE ገጽ 172-173 የተገኘ ነው። HODDER & STOUGHTON 1995 A.D. ።

(3) TERTULLIAN በ NIDCC ።

(4) የሰባልዮስ ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ SABELLIANISM ወይም MODALISM ይባላል። UNITARIANISM ና MONARCHIANISM የተባሉ ትምህርቶች ደግሞ በአነሣሣቸው ከሰባልዮስ ትምህርት ጋር አንድ ናቸው። NIDCC በየርእሱ ይመ.

(5) በ NIDCC ARIANISM, ATHANASIUS, NICEA, COUNCIL OF (325), NICENE CREED ይመ.

(6) በNIDCC 'JEHOVAH'S WITNESSES'፤ ት.መ. ገጽ 40-46።

(7) D.T. ገጽ 147 ማስታወሻ 3።

(8) D.T. ገጽ 156-157።

(9) ስለ ንድፎችና ማብራሪያዎች GERALD BRAY በ D.G. በተለይ ገጽ 157 እና 174 ይመ.

(10) GRUDEM ገጽ 246፤ NIDCC "PROCESSION OF THE SPIRIT" ይመ.

(11) D.G. ገጽ 180-181።

(12) D.G. ገጽ 182-184።

(13) D.G. ገጽ 185-189።

(14) ስለ ካልቪን ትምህርት በ D.G. ገጽ 199-206 በዐጭር ማብራሪያ ተመሥርቷል።

(15) ከመሠረት ስብሐት ለአብ በ«ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ» በ1951 ዓ.ም. የታተመ ገጽ 39።

(16) ስለ ካርል ባርት (BARTH, KARL በ NIDCC) D.G. ገጽ 189-195 ዐጭር ማብራሪያ ተመሥርቷል።

(17) NIDCC "APOSTLES CREED" ይመ.፤ ይህ ትርጉም ከ«ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ» ገጽ 32 የተቀዳ ነው።

(18) NIDCC "NICENE CREED" ይመ፤ ይህ ትርጉም ከ«ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ» ገጽ.32 የተቀዳ ነው።

(19) NIDCC "ATHANASIAN CREED" ይመ.፤ ይህ ትርጉም ከ«ስምዓ ጽድቅ ብሔራዊ» ገጽ 38 የተቀዳ ነው።

(20) እ.ት. ገጽ 62-63።

(21) NIDCC NICEA, COUNCIL OF (325) ይመ.

# ምዕራፍ 28 - ትምህርተ ሥላሴ በክርስቲያናዊ ኑሮ

አንዳንዶች ትምህርተ ሥላሴን መከራከሪያ ያደርጉታል፤ ከእንደነዚህ ሰዎች ጋር መነጋገር ዋጋ የለውም። እኛ ግን ትምህርተ ሥላሴ ለትምህርተ መለኮት ሁሉ አጠቃላይ ዋስትና መሆኑን እናውቃለን፤ ደግሞም በእግዚአብሔር መልክ ስለተፈጠርን የሦስቱ አካላት ኅብረት ለሰው ኅብረት፥ የእያንዳንዱ አካል አካልነት ደግሞ ለሰው አካልነት ምሳሌ እንደሆኑ እንቈጥራቸዋለን። እንግዲህ በክርስቲያናዊ ኑሮ የትምህርተ ሥላሴን አስፈላጊነት በአራት አርእስት አካትተን ለማየት እንሞክር።

## ሀ) ትምህርተ ሥላሴ ሰውን ከብዙ ስሕተት ይጠብቃል (1)

ስሕተት በየጊዜው በቤተ ክርስቲያን ይነሣል፤ ስሕተቶቹ በልዩ ልዩ መልክ ቢገለጡም፥ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ከትምህርተ ሥላሴ ጋር አይስማሙም።

1. ትምህርተ ሥላሴ ሰው የሆነው ከዘለዓለም የነበረ ወልድ በመሆኑ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ያረጋግጣል። ይህንም ሲያደርግ፥ የሰባልዮስንና የሦስት አማልክትን ትምህርቶች ያፈርሳል።

2. ትምህርተ ሥላሴ የእግዚአብሔርን አንድነት ይጠብቃል። በዚህም ወልድ ፍጡር ነው የሚለውን የአርዮስን የኑፋቄ ትምህርት ያፈርሳል።

3. ትምህርተ ሥላሴ በእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርና በአካላዊ ሕይወት ዘለዓለማዊነትን ይጠብቃል። ይህንም ሲያደርግ፥ ፍጥረት ዘለዓለማዊ ወይም እግዚአብሔር በግዴታ የሚፈጥረው መሆኑን ከማሰብ ይጠብቃል።

4. ትምህርተ ሥላሴ የደኅንነትን ዕቅድ ይጠብቃል። በዚህም ሦስቱ አካላት በአንድነት ሲፈቅዱ፥ የአብን መወሰንና መምረጥ፥ የወልድን ማስታረቅና መዋጀት፥ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወትን የመስጠትና የመቀደስ ምግባሮች ይጠብቃል።

ትምህርተ ሥላሴ ለክርስቶስ ወንጌል መሠረት ነው፤ ይህም ማለት ትምህርተ ሥላሴ የተገኘው ልዩ ልዩ ስሕተትን ለመቃወም ሳይሆን፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያቱ የሰበኩት መልእክት ምንጭና መሠረት ማለት ነው። ትምህርተ ሥላሴ ከሐዋርያት ስብከት በስተጀርባ ነበረና በትምህርተ መለኮት ላይ የተነሣው ክርክር በግልጽ አሳየው።

ትምህርተ ሥላሴ ከዚህ በላይ ያለውን ስፍራ ካልያዘ በክርስቲያናዊ ኑሮ ከሚታዩ ሁለት የተዛቡ አመለካከቶች መካከል አንዱ ይገኛል፤ እነርሱም፥ አንደኛው የፍጥረትን ሁኔታ፥ የግብረገባዊነትን መለኪያዎችና የቅድስናን ሥርዐት የማይመለከት «መንፈሳዊ» ሃይማኖት ሲሆን፥ ሁለተኛው ቤዛነትንና ዳግመኛ መወለድን የማይመለከት ተፈጥሮአዊ ሃይማኖት ነው።

## ለ) ትምህርተ ሥላሴ የጸሎትን መንገድ ያሳያል

ክርስቲያን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በመጠመቁ ከሦስቱ አካላት ጋር ግንኙነት እንዳለው ይታመናል። እንግዲህ አማኙ ሲጸልይ የማንን ስም መጥራት ይገባዋል? ሦስቱ በህላዌ፥ በባሕርይ፥ በመለኮት አንድ ሲሆኑ በአጠራርና በአካልነት ቅደም ተከተል እንዳላቸው አይተናል። አብ፥ አባት እንደመሆኑ መጠን ለስም አጠራር ቅድሚያ አለው። ክርስቶስ፥ «አባታችን ሆይ...» ብሎ ደቀ መዛሙርቱን እንዲጸልዩ

ያዘዛቸው ከዚህ ጋር ይስማማል። እንደዚሁም ለእግዚአብሔር ጸጋ የክርስቲያን አጸፋ «አባ አባት ...» ወይም «እግዚአብሔር አባ አባት ...» የሚለው የልጅነት መንፈስ ነው፤ ሮም 8፥15፤ ገላ. 4፥6። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጸሎቱ ሲያሳስበን፥ «... በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ» ይላል፤ ኤፌ. 3፥14-15። በአርአያውና በትምህርቱ ክርስቲያን የአብን ስም እንዲጠራ ያስገነዝባል፤ ኤፌ. 1፥3፤ 2፥18፤ 5፥20፤ ፊል. 4፥20፤ ቆላ. 1፥3-5:12፤ 3፥17። ሆኖም ክርስቲያን «አብ» ብሎ ሲጸልይ አብ የወልድ አባት መሆኑን ያሳስበናል፤ ለምሳሌ፥ «... የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ» ብሎ ያመሰግናል፤ ኤፌ. 1፥3። ይህም ብቻ ሳይሆን ለአብ ሲጸልይ በልጁ አማካይነት ወደ አብ እንደሚቀርብ ይገነዘባል (ኤፌ. 5፥20፤ ቆላ. 3፥17)፤ ምክንያቱም ለአብ የሚጸልየው በክርስቶስ ስም ነው፤ ዮሐ. 16፥23-24።

በአጠቃላይ አስተያየት በጸሎት ወደ አብ እንድንቀርብ ተመርተናል። ይህ ማለት ወደ ወልድ መቅረብ አይገባም ማለት አይደለም። ክርስቶስ፥ «ወደ እኔ ኑ ...»፤ «...ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም» የሚሉትና የመሳሰሉ ጥቅሶች በምድራዊ አገልግሎት አይወሰኑም፤ ማቴ. 11፥28፤ ዮሐ. 6፥37። ደግሞም፥ «ማንም ... ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ» የሚለውን የተስፋ ቃል ከሰማይ ሰጥቷል፤ ራእ. 3፥20። ሐዋርያትም፥ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» ብለው ላልዳኑት ተስፋ ሰጥተዋል፤ ሐ.ሥ. 2፥21፤ ሮም 10፥13። ምናልባት፥ ሰው እንዲድን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሲሄድ፥ የክርስቶስን ስም ይጠራ ይሆናል፤ ከዚያም በኋላ የክርስቶስ መሆኑን ዐውቆ በክርስቶስ አማካይነት (ስም) ወደ አብ ስለሚቀርብ፥ የአብን ስም በድፍረት መጥራት ይችላል ማለት ይገባናል።

መንፈስ ቅዱስ እንድንጸልይ ይቀሰቅሰናል። ክርስቲያን በብዙ ስፍራ፥ በብዙ ሁኔታ፥ በልዩ ልዩ ሰዓት መጸለይ እንደሚገባው ወይም እንደሚፈልግ ይሰማዋል። ከዚህ የተነሣ ለአብ ወይም ለወልድ ይናገራል። ይህም ስሜት ከመንፈስ ቅዱስ እንደተገኘ ያውቃል። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን በልዩ ልዩ ጥቅሶች እናያለን፤ ለምሳሌ በሮም 8፥15-16:26፤ ገላ. 4፥6። ክርስቲያን ለመንፈስ ቅዱስ መጸለይ ይገባዋል? ሰው ይህን ሲያደርግ ወይም እንዲያደርግ ሲታዘዝ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ አልተጻፈም። ሆኖም በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፥14 በመልእክቱ መደምደሚያ የሚገኘው፥ «... የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን» የሚለው የሐዋርያው ምኞት ከጸሎት የወጣ አይደለም። በራእይ 1፥4-6 ስለ ሰባቱ መናፍስት ሐዋርያው ዮሐንስ የተናገረውም የጸሎት መንፈስ እንዳለበት ግልጥ ነው። አበው ጸሎታቸውን ያቀረቡት ለአብና ለወልድ እንጂ ለመንፈስ ቅዱስ አልነበረም። ከእነርሱም በኋላ ቤተ ክርስቲያን መዝሙሮችንና ጸሎቶችን ለመንፈስ ቅዱስ አቅርባለች። መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነውና ወደ እርሱ መጸለይ ስሕተት ሊሆን አይችልም፤ ሆኖም አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስን መምሪያ መከተል ይገባናል። የጸሎት ምሥጢር «ለአብ፥ በወልድ አማካይነት፥ በመንፈስ ቅዱስ ቀስቃሽነት» በሚለው ሐረግ እንደሚገኝ በብዙ ሊቃውንት ይታመናል(2)።

## ሐ) ትምህርተ ሥላሴ አካልነትን ይገልጣል

አካልነትን ለመወሰን ብዙ ሙከራ እንደተደረገ አይተናል፤ በ4ኛው ጥናታችን በ«ትምህርተ ሰብእ» ወደዚህ አሳብ ሳንመለስ አንቀርም። የሰው አካልነት ከእግዚአብሔር የተገኘ በመሆኑ (ኤፌ. 3፥14-15) ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሯል፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዘንድና በሰው ዘንድ ያለው አካልነት ሙሉ በሙሉ

አንድ ባይሆንም፥ ተመሳሳይነት አለና ለሰው አካልነት የእግዚአብሔር አካልነት ዐቢይ ምሳሌ ነው። ይህንም ስንል የእግዚአብሔር አካልነት ፍጹም ሲሆን፥ የሰው አካልነት ግን ፍጡር በመሆኑ ውሱንና ኀጢአተኛ በመሆኑ የተዛባ እንደሆነ መገንዘብ አለብን። የእግዚአብሔርን አካልነት ስንመለከት ቢያንስ ሦስት ታላላቅ አሳቦችን እናገኛለን ፡-

1. ኅብረታዊ ኑሮ

በም. 26መ የሦስቱን አካላት ግንኙነት መረመርን። በእነርሱ ዘንድ እያንዳንዱ በሌሎች ውስጥ ይኖራል፤ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት ህልውናቸው አንድ በመሆኑ ነው። በሰው ዘንድ ግን እያንዳንዱ ሰው የራሱ ህልውና አለው። አስቀድመን እንደገለጥነው ግን የአንድ አካል አካላዊነት በተወሰነ አቅጣጫ የሚታየው ከሌሎች አካላት ጋር በመገናኘት፥ በመሥራት፥ አሳብን በመለዋወጥ ... ወዘተ ነው (ም.25 መ1)። ይህ ኅብረታዊ ኑሮ በቅድስት ሥላሴ ውስጥ በፍጹምነት ይታያል። እነርሱ አንድ ባሕርይ፥ አንድ ፈቃድና አንድ ዕቅድ አላቸው። ቢሆንም እያንዳንዱ አካል የራሱ አካላዊነት አለው (ም. 26ሐ)።

በኅብረታዊ ኑሮ የሁለት ነገሮች ጐን ለጐን መሄድ አስፈላጊ ነው፤ እነርሱም የአካላት አንድነትና የእያንዳንዱ አካል የግል መብት ናቸው። በቅድስት ሥላሴ ይህ ተቃርኖን አያመጣም፤ ምክንያቱም ፈቃዳቸው አንድ ነው። በሰዎች ዘንድ ግን ሁልጊዜ ውጥረት አለና በማኅበሩና በእያንዳንዱ አባል መካከል ያለው መብት ሚዛናዊ መሆን አለበት። ይህ ማለት፥ በሥላሴ ዘንድ ሦስቱ ሁሉን በውዴታ ሲያደርጉ፥ በሰው ኅብረታዊ ኑሮ ግን የተወሰኑ ሰዎች ጥቂት ነገሮችን በውዴታ ሲፈጽሙ፥ ሌሎች በግዴታ ወይም አንድነት እንዳይጠፋ የራሳቸውን የግል ፈቃድ ለአንድነቱ ያስገዛሉ።

ክርስቲያኖች በክርስቶስ ሆነው ወደ ፈቃዱ እየቀረቡ በመሄዳቸው ወደ አንድ አሳብ እየተቀራረቡ ይኖራሉና በመካከላቸው ያለው ውጥረት እየቀነሰና አንድነታቸው እየጠነከረ ይሄዳል። እያንዳንዱ አማኝም ስፍራውን በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አግኝቶ ብስለት ወዳለው አካልነት ያድጋል፤ 1ጴጥ. 1፥5፤ ኤፌ. 4፥12-13።

2. ነጻነት

ክርስቶስ ነፍሱን ለማኖርና ለማንሣት ሥልጣን ነበረው፤ ይህንም በፈቃዱ አድርጎታል፤ ስለዚህ አብ ይወደዋል፤ ዮሐ. 10፥17-18። እውነተኛ ነጻነት ሰው ያለ አንዳች ክልከላ የሚመቸውንና የሚፈልገውን ማድረግ ሳይሆን፥ የሚገባውን የማድረግ ችሎታ ሲያገኝ በውዴታ መፈጸም ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእውነተኛ ነጻነት ፈጻሚ በመሆን ዐቢይ ምሳሌ ነው።

ክርስቶስ ተገቢውን ለመፈጸም መሥዋዕትነት ጠየቀው፤ ሕይወቱንም በመስጠቱ አብ ደስ ተሰኘበት። ሰው በክርስቶስ ነጻነት ሲኖረው፥ ጊዜውን፥ ገንዘቡን፥ ሕይወቱንም እንኳ በመስጠት የክርስቶስን አርአያ ይከተላል።

*መሥዋዕትነት*፥ ሰው ሌሎች ነገሮችን ትቶ ለአንድ ዓላማ ራሱን አሳልፎ መስጠቱን ያሳያል። ክርስቶስ በኀጢአን ለማዳን ራሱን አሳልፎ ሰጠ። በክርስቶስ ያሉ ሁሉ የጌታቸው ዓላማ እንዲፈጸም እንደሚመራቸው በመሥዋዕትነት ይኖራሉ።

ክርስቶስ መሥዋዕቱን ሲያቀርብ አብና መንፈስ ቅዱስ አብረውት እንደነበሩ ገልጠናል (ም.26 ለ1)። እንደዚሁም አማኝ በመሥዋዕትነት ሲሠራ ብቻውን አይደለም። ሌሎችም በሥራው ከእርሱ ጋር ይኖራሉ። ምእመናን አብረው ሲሠሩ፥ አንድ መሪና አዛዥ ይኖራቸዋል። ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሲሠሩም፥ በደስታ የተቀበሉትን የአብን ዕቅድ ይከተላሉ፤ ይፈጽሟሉም። መንፈስ ቅዱስም በወልድ ዘንድ

ያለውን እንደተቀበለ፥ ራሱን ሳይሆን ክርስቶስን ከፍ ከፍ እንደሚያደርግ አይተናል (ም. 26ሐ)። አንዳንድ ጊዜ ሰው ለመሪነት ብቃት እንዳለው ይሰማዋል፤ ነገር ግን ሌላ ሰው ከበላዩ ይሾማልና ይህን በትሕትና መቀበል ለእርሱ መሥዋዕትነት ይሆናል።

3. አካላዊነት

አንድ ክርስቲያን በማለዳ ተነሥቶ መጽሐፍ ቅዱስን ያነባል፤ ይጸልያልምና እግዚአብሔርን በዚህ መንገድ ከማወቅ የበለጠ ነገር እንደሌለ ያስባል። ከዚያም ቀጥሎ ወደ ትምህርት ይሄዳልና ትምህርቱን ተከታትሎ እውነትን መረዳት እንዴት ያለ አስደሳች ነገር ነው ብሎ ሊገረም ይችላል። ከአንዲት መልከ መልካም ሴት ጋር ምሳ ይበላልና ከእርሷ ጋር መገኘቱም ከአሳቡ የተወሰነውን ያስቀራል። ከሰዓት በኋላ ቢሮ ገብቶ ድርጅቱን ያስተዳድራልና ሌሎች ሰዎችን በጥሩ አኳኋን ከመምራትና ከማስተዳደር የበለጠ አገልግሎት የሌለ ይመስለዋል። ከዚያ ቀጥሎ ወደ ኪነ ጥበብ ትምህርት ቤት ሄዶ ሥዕል ይሥላልና ከዓለም እውነት መሠረት ጋር ለመገናኘት ይመኛል። ማታም ከጓደኞቹ ጋር አብሮ እራት ይበላል፤ ይጫወታል፤ ይሥቃልና ይህ በእውነት ሕይወት ነው ብሎ ወደ ቤቱ ይመለሳል።

ችግሩ ሰው እነዚህን መልካም ነገሮች ሁሉ መከታተል አይችልም! ክርስቲያን በእግዚአብሔር የተሰጠውን ታላቅ አገልግሎት ዐውቆ እንደ ሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል እነዚህን ነገሮች በመሥዋዕትነት ሊተው ይገባል። በወንጌል ምክንያት ጋብቻን ወይም ኪነ ጥበብን ወይም ከጓደኛ ጋር መጫወትን ወይም እስፖርትን ወይም ሌላ ነገርን ይተዋል። እነዚህን ነገሮች ለእግዚአብሔር ያስረክባልና ሌሎች ሰዎች እነዚህን መከተል ሲችሉ ደስ ይሰኛል። በዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐቢዩ ምሳሌ ነው፤ እርሱ ሁብታም ሆኖ ሳለ ለእኛ ብሎ ድኻ ሆኗልና፤ 2ቆሮ. 8፥9፤ ዮሐ. 17፥5። ክርስቲያን በዚህ ምሳሌነት ጌታውን ሲከተል አካላዊነቱን ያዳብራል።

መ) ትምህርተ ሥላሴ ዘለዓለማዊነትን ያብራራል (4)

በህንድ አገር በአንድ አምላክ የሚያምኑ የእርሱ አንድነት ምሥጢራዊነት ያለበት ሳይሆን በስሌት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያስባሉ። ስለዚህ ለሰው ዋናው ተስፋ በአምላኩ አንድነት መመሰጥ ነው፤ እዚያም ሁሉ አንድ በመሆኑ የሰው አካላዊነት ይቀራል።

ክርስቲያን ግን ስለ እግዚአብሔር አንድነት ሲያስብ አንድነቱ ምሥጢራዊነት ያለበት ይሆናል፤ ም. 25 መ2 ይመ.። ከዚህም የተነሣ ስለ ዘለዓለም ሕይወት ያለው ተስፋ ከፍ ያለ ነው፤ ይኸውም በትንሣኤው ዕለት ሥጋውና ነፍሱ እንደገና ተዋሕደው ፍጹም አካላዊነት ይኖረዋል፤ እርሱ ጓደኞቹን፥ ጓደኞቹም እርሱን እያዩ ይደሰታሉ፤ 1ተሰ. 2፥19። እንግዲህ የክርስቲያን ዘለዓለማዊ ተስፋ ከእግዚአብሔር አንድነት ጋር እንደሚያያዝ በሚከተለው አንቀጽ ይገለጣል ፦

«ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደወደድሃቸው ያውቃል። አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ»፤ ዮሐ. 17፥20-24።

«እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ» የሚለው ሐረግ የሥላሴን የባሕርይና የህልውና አንድነትና የምእመናንን ሰማያዊ አንድነት ተመሳሳይነት ያንጸባርቃል፤ ክርስቶስም «ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ» በማለቱ የምእመናን አንድነት በእርሱ መሆኑን ያሳያል። የእግዚአብሔር አንድነት የእውነተኛ አንድነት ሁሉ ዐቢይ ምሳሌ ነው። አምላካዊው ፍቅር ለዘለዓለም የሦስቱን አንድነት እየጠበቀ የእያንዳንዱን አካላዊነት ያከብራል። ምእመናን ሁሉ በዚያ ሕይወት ሲሳተፉ፥ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ምእመናን ሁሉ ጋር አንድ ሲሆኑ፥ የእያንዳንዱ አካላዊነት ተጠብቆ ይከበራል፤ በእግዚአብሔር ዐይን የእያንዳንዱ ሰው ልዩ አካላዊነት ዋጋ ያለው ነውና። ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ ለዚህ ክብር እያዘጋጀን ቈይቷል፤ ከሰው አስተሳሰብ እጅግ በላቀ መንገድም በዘለዓለም መንግሥቱ ዕቅዱን ይፈጽማል። ስለዚህ ቅድስት ሥላሴ የተመሰገነ ይሁን!

## ማስታወሻ

(1) ይህ ክፍል ካልታተሙት የዶክተር J.I. PACKER የትምህርት ማስታወሻዎች የተገኘ ነው።

(2) "UNDERSTANDING DOCTRINE" በALISTER McGRATH ገጽ 175 በHODDER AND STOUGHTON 2ኛው እትም 1990 ዓ.ም.።

(3) ይህ ክፍል ከ D.T. ገጽ 183-187 በዐጭሩ የተገኘ ነው።

(4) ይህ ክፍል ከ D.T. ገጽ 187-189 በዐጭሩ የተገኘ ነው።